# የግብረገብ ትምህርት

## የመምህራን መምሪያ

## 4ኛ ክፍል

**ተርጓሚዎች**

እየሩሳለም ገርባባ

ስሪቃ ገመቹ

አበባየሁ ደምሴ

**የአርታዒ**

በቀለ ቀነኣ

ረታ ነገዎ

ደጀነ ታፈሰ

**ግራፍክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገምጋሚ**

ደረጀ መኮንን

**© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023**

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።

## ምስጋና

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው። በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ። በመሆኑም በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው።

# ማውጫ


ይዘት ገጽ

መግቢያ ........ v

ምዕራፍ 1፡ ራሰን መሆንን ማጎልበት ........ 1

1.1. ራስን መሆን ........ 1

1.2.ራስን የመሆን ባህሪያት ........ 4

1.3. በራስ መኩራትን ማዳበር የሚቻልባቸው መንገዶች ........ 13

1.4. በራስ የመኩራት ጥቅሞች ........ 15

1.5. ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ ........ 17

1.6. ራስን ያለመሆን ውጤቶች ........ 20

ምዕራፍ 2፡ ሰብአዊ መብቶች ........ 23

2.1. ሰብአዊ መብቶች ........ 23

2.2. የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ........ 27

2.3. ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች ........ 30

2.4. ሰብአዊ ክብር ........ 34

2.5. የሕፃናት መብቶች መከበር ........ 37

2.6. የሴቶች መብት መከበር ........ 40

2.7. የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር ........ 43

ምዕራፍ 3፡ ሰላም ........ 48

3.1 የሰላም ምንነት ........ 48

3.2. የሰላም አስፈላጊነት ........ 51

3.3 ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶች ........ 53

3.4 ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፈታት ........ 56

3.5. የሰላም እጦት የሚያስከትለው ጉዳት ........ 59

ምዕራፍ 4: በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚያስፈልግ ሥነ-ምግባር ......... 61

4.1. የሥነ-ምግባር ምንነት ......... 61
4.2. በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሥነ-ምግባር አስፈላጊነት ......... 66
4.3. የእረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ......... 69
4.4. በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት ..72
4.5. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ......... 76
4.6. በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚያስፈልጉ የሥነ-ምግባር መርሆዎች.........78

ምዕራፍ 5፡ የመቻቻል ባሕል ......... 82

5.1. የመቻቻል ባሕል ምንነት ......... 82
5.2. የመቻቻል ባህል መገለጫዎች ......... 84
5.3. የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት ......... 86
5.4. በመቻቻል ውስጥ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ......... 88

ምዕራፍ 6 ፡ የባህል ብዝሃነትን ማክበር_ ......... 91

6.1. የባህል ብዝሃነትን ማክበር ......... 91
6.2. በባህል ልዩነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት ......... 94
6.3. በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል ጥቅሞች ......... 96
6.4. የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ ......... 98

የግብረገብ ትምህርት 4ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት ......... 101

**መግቢያ**

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየው በማሰብ ችሎታውና በማህበራዊ ባህሪው ነው። እነዚህ ባህሪያታ ደግሞ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ናቸው። ሰዎች የህብረተሰቡን የመልካም ስነምግባር እና የሞራል መመሪያዎችን በመከተል ባህሪያቸውን ያሳያሉ። እነዚህ ባህሪያት ከሌሎች የሚኮረጁ ሳይሆን ከራሳቸው ከሰዎች አእምሮ የሚገኝ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት የሚለየው በማህበራዊ ባህሪውና በምክንያታዊ አስተሳስቡ ነው። ይህም የሰው ልጆች የመልካም ስነ ምግባና ሞራል መመሪያዎችን እንዲከተሉ ያደርጋቸዋል።

መልካም ሥነ ምግባርና ግብረ ገብነት እውነትን በመከተል እና የሰው ልጆች በሰላም አብሮ የሚኖሩበትን መንገድ የሚያሳይ ነው። ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሆነ መደበኛና ትክክለኛ የሆነ ባህሪይ የሚቆጣጠርበት መንገድ አለው። መልካም ሥነ ምግባር ሰዎች ማህበራዊ እሴቶቻቸውን እንዲማሩና እንዲተገብሩት ያስገድዳቸዋል። ስለዚህ ህበረተሰቡ የማህበራዊ እሴቶቹን እንዲሠራ በማድረግ የባህሪይ መመሪያዎች ሆነው ያገለግላሉ። ማንኛውም ማህበረሰብ ህልውናውን ለማስቀጠል ማህበራዊ እሴቶቹንና መልካም ስነ ምግባሩን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ይኖርበታል። ይህ ማለት ደግሞ ሰዎች የማህበረሰቡን እሴቶች ሲማሩ ለሥነምግባርና ለሥነ ሥርዓት የመታዘዝ ፍላጎት ያዳብራሉ። መልካም ስነ ምግባር የማህበራዊ ባህሪ መመሪያ ስለሆነ መደረግ ያለበትንና የሌለበትን እሴት ይደነግጋል።

መልካም ሥነ ምግባር አምስት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት። እነሱም:-

1. የማህበረሰቡን ወጎችና መልካም ሥነ ምግባርን ማስቀጠል፣

2. የሰው ልጅን ችግር ለመፍታት፣

3. የሰው ልጅን ዕድገት ደረጃ ማስቀጠል፣

4. ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታና፣

5. ምክንያታዊ የሆነ ፍርድ ለመስጠት ነው።

በአጠቃላይ መልካም ሥነ-ምግባር የማህበራዊ መርሆዎች ስብስብ ሆኖ ወደ አንድ የጋራ ግብ የሚያመራ ነው። የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት ለሰው ልጅ ህይወት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ስነ-ምግባር ከበፊቱ በተሻለ መንገድ አጥብቀን መያዝ አለብን። ይህ ትምህርት መልካም ስነምግባርን ህግን፣ ደግነትንና መከባበርን፣ ታማኝነትን፣ ራስን መግዛትን፣ ድፍረትን፣ ወዳጅትንና ትህትናን ለማስተማር ይረዳል። በተጨማሪም የሰው ልጆች ጥሩ ህይወት እንዲመሩ፣ እንዲግባቡና ከሌሎች ጋር በሰላም እንዲኖሩ የግል መልካም ሥነ ምግባራዊ ባህሪያትን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

የስነምግባር ትምህርት ዓላማ በተማሪዎች ባህሪ እና የአመለካከት ለውጦች እንዲመጡ በማድረግ ማህበራዊ መልካም ስነምግባርን እንዲማሩ እና እንዲያዳብሩ እንዲሁም በህይወታቸው እንዲተገበሩ ማድረግ ነው። በዛሬይቷ ኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ውስጥ የስነ-ምግባር ትምህርት ከ1-6ኛ ክፍል ራሱን የቻለ የትምህርት ዓይነት ሆኖ እንዲሰጥ በግልፅ ተቀምጧል። በ4ኛ ክፍል የስነ ምግባር ትምህርት ውስጥም በራስ መተማመን፣ሰብአዊ መብት ማክበርን ፣የራስን ሃላፊነት መወጣትን፣ ቻይነትን፣መልካም መልካም

ስነምግባርን ፣ሰላምን፣መተባበርንና ማከበር እንዲሁም የባህል ብዝሃነትን በማክበር እውቅና መስጠትን አጠቃሎ የያዘ ነው።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

በ4ኛ ክፍል የስነ-ምግባር ትምህርት ትግበራ ውስጥ ተማሪን ያማከለ የመማርና ማስተማር ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ነው። አሳታፍ የመማር ማስተማር ዘዴ ተማሪዎች በቡድን ወይም በግል በይዘትና በዋና ዋና ሀሳቦች ላይ በማተኮር ስኬታማ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል። በተጨማሪም በተማሪዎች መካከል ጥሩ ግንኙነት ለመፍጠርና የተማሪዎችን የመግባባት ችሎታ ለማሻሻል ይረዳል። አሳታፍ የመማር ማስተማር ዘዴ ተማሪዎች በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያዳብሩና ለሚማሩት ትምህርት አዎንታዊ አመለካከትን እንዲሰጡ ያበረታታቸዋል።

ይህ የመምህሩ መመሪያ  አሳታፍ የመማር ማስተማር ዘዴንና  ተማሪን ያማከለ አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል፣ ተማሪዎችም በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታታቸዋል።  ይህም ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው ብዙ ትግበራዎችን እንዲሰሩ  ያግዛቸዋል። ለምሳሌ ለተወሰነ ተግባር ራሱን ችሎ መረጃ መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ ማቅረብና ለክፍሉ ጓደኞቹ/ቿ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም በቡድን ስራ ውስጥ በንቃት በመሳተፍና የሚታዩትን ዋና ዋና ሀሳቦችን በማቀናጀት ለክፍል ጓደኞቻቸው ማስረዳት ይረዳቸዋል። ተማሪዎች የጉዳይ ጥናት ሀሳቦችንንና ትረካዎችን አደራጅተው ለቡድናቸው ወይም ለክፍላቸው ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን መምህሩ/ሯ ደግሞ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል/ባታል።

- ሁሉም የየቡድን አባላት አንድ በአንድ ሃሳባቸውን እንድገልጹ ማበረታታት፤
- ተማሪዎች ርዕሶቻቸውን እንድገልጹ እድል መስጠት፤
- በጾታ እኩልነትና አካል ጉዳተኞችን በማበረታታት ላይ ማተኮር ።

☞ በዚህ የመማር ማስተማር ዘዴ ውስጥ የመምህሩ ሚና ተማሪዎችን የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ መምራትና ማመቻቸት ነው።

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

መምህር፣ አዲስ ርዕስ ስጀሚሩ የግንዛቤ ጥያቄዎችን ይጠቀሙ። ይህም ተማሪዎች ስለ ርዕሱ የሚያውቁትን ሁሉ እንዲናገሩና ስለሚማሩት አዲስ ርዕስ እንዲያስቡ ያስችላቸዋል። እንዲሁም ከርዕሱ ጋር የተያያዙ አጠቃላይ ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

**ማንበብ**

ከሥነ ምግባር ትምህርት ጋር የተያያዙ ጽንሰ-ሐሳቦችን በተጨማሪ ጽሑፎች ውስጥ መፈለግና ማንበብ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ በሞራል፣ በሥነ ምግባር፣ በማኅበራዊ፣ በሂሳዊ አስተሳሰብ፣ በዕለት ተዕለት ህይወት ችሎታዎች፣ በተለያዩ ባህሎች ላይ የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ ወሳኝ ነው።

**የጉዳይ ጥናት**

በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን ትረካዎችእና የጉዳይ ጥናቶች በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ የመልካም ስነ ምግባር ፅንሰ-ሀሳቦችን እውነተኛ በህሪይ ያሳያሉ። ስለዚህ ይህ የ4ኛ ክፍል የግብረ ገብ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍ

እንዴት እንደሚተገበር የሚያሳይና መምህራንን ለመርዳት ተጨማሪ መረጃ ይዟል።

**ጥያቀ እና መልስ**

የጥያቄ እና መልስ አቀራረብን መጠቀም ዕለታዊ ትምህርትን ለመግለጽ ወሳኝ ነው። በውይይቱ ወቅትና ከዛ በፊት ይህንን ዘዴ መጠቀም ጥሩ ነው። በሚጠቀሙበት ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች ለመናገር ዕድል እንዲያገኙ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ይህ ዘዴ መምህሩ የተማሪዎችን የተሳትፎና የግንዛቤ ደረጃቸውን ለመፈተሽ ይረዳል።

የጥያቄ እና መልስ ዘዴን ለመጠቀም የሚያሰችሉ ስልቶች፡

- ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ አጠቃላይ ክፍሉን በእይታ መከታተልና ተማሪዎች በተናጠል እንዲመልሱ ማድረግ ናቸው። የተማሪ ተሳትፎን ማበረታታትና ጥያቄው ከባድ ከሆነ፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በዝርዝር በመፃፍ መግለጽ። በጥያቄ እና መልስ ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም አስፈላጊ ነው።
    - ጥያቄውን አጭርና ቀለል ማድርግ
    - በተቻለ መጠን ሁሉንም ተማሪዎች ማዕከል ያደረጉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይህም ነጠላ ጥያቄዎችን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅን ያካትታል (ሁሉም መለሰተኛ፣ መካከለኛ እና በጣም ጠንካራ ተማሪዎች ማለት ነው)
    - ጥሩ ተሳትፎ ያላቸውን ተማሪዎች ማድነቅ፣ ማንቃት፣ መሸለም፣ እና ሌሎች ስልቶችን በመጠቀም ማበረታታት ናቸው።

**የቡድን ውይይት**

የቡድን ውይይቶች በጥንድ ወይም በትናንሽ ቡድኖች ወይም በአጠቃላይ ክፍል ልደረጉ ይችላሉ። አጠቃላይ የክፍል ውሰጥ ውይይቶች የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማመቻቸት ይረዳሉ።በየምዕራፉ ተማሪዎች በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ተማሪዎች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቡድን ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው።

- ሁሉም ተማሪዎች በቡድኑ ውስጥ እየተሳተፉ መሆናቸውንና እንዴት እንደሚሳተፉ መከታተል
- የተወሰኑ ቡድኖችን በመመልከትና በመከታተል ትክክለኛ መንገድ ላይ መሆናቸውን ማረጋግጥ
- ተማሪዎች በቡድን ውይይት ውስጥ ሃሳብ ከተምታታባቸው አቅጣጫ መጠቆም
- ተማሪዎችን በቡድን ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መምራት
- እያንዳንዱን ተማሪ በቡድን ውይይት ውስጥ ምን ያህል እንደሚሳተፍ በመመልከት፣ አነስተኛ ተሳትፎ ያላቸውን ተማሪዎች በማበረታታትና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ክህሎቶቻቸሁን ተጠቅመው መርዳትና ማበረታታት ።

## ቡድኖችን ማደራጀት

በዕለቱ የትምህርት ርዕስ እና ተግባራት ላይ በመመስረት ቡድኖችን ያደራጁ። ተማሪዎችን በቡድን በሚያደራጁበት ጊዜ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ።በዚህ መሠረት የሚከተለውን ዘዴ መጠቀም አሰፈላጊነው ።

- በክፍል ውስጥ ባሉ የተማሪዎች ብዛት ላይ በመመስረት አነስተኛ የቡድን ውይይት ዘዴን መፍጠር።
- ተማሪዎች እርስበርስ እንዲተያዩ የመቀመጫ ወንበራቸውን በክብ ማበጀት።
- ሊያወያዩ የሚችሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ መዘጋጀት ልረዱ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- ተማሪዎች እንዲሰሩ ያዘጋጁትን መንገር።
- እያንዳንዱ ቡድን የቡድን መሪ እና ጸሐፊ እንዲመርጥ ማድረግ እያንዳንዱ ተማሪ ቡድኑን የመምራት ዕድል እንዲያገኝ ማድረግ ።
- ለተማሪዎች የተሰጠውን የቡድን ውይይት በምን ያህል ጊዜ ማጠናቀቅ እንዳለባቸው መንገር።
- ለእያንዳንዱ የሰሩትን የቡድን እንዲያቀርቡ ዕድል መስጠት። በመጨረሻም ከቡድኖቹ ውይይት የቀረቡትን ሃሳቦች ማረምና ማጠናከር አለበት።

## አካታችነት

ማንኛውም የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ የተማሪዎችን በፆታ ልዩነት, በልዩ ስጦታዎችና ችሎታዎች, እንዲሁም የተለያዩ የአካል ጉዳተኝነት ደረጃዎችን

ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት። እንዲሁም ተማሪዎች ልዩነቶች እንዳሉ እንዲገነዘቡና በመከባበርና በመግባባትና በስምምነት አብረው በመማር ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማበረታታት።ተማሪዎች በመማር ማስተማር ውስጥ ያሉትን ችግሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ እንዲሁም የትብብር ግንኙነቶችን እንዲያዳብሩ ማበረታታት።

## ተጨማሪ ትግበራ

እያንዳንዱ ተማሪ የተሰጠውን የተግባር ስራ እንዲረዳ ለማገዝ ተጨማሪ ተግባራት ጥቅም ላይ ማዋልና ተግባራቶቹን በመከተል ግብረመልስ መሰጠት አለበት። ለምሳሌ፣ ራስን መሆንን በተመለከተ ለመወያየት፣ ተጨማሪ ተግባራት ያስፈልጋሉ።

## አጫጭር ማሰታወሻዎችን መስጠት

እንደ አስፈላጊነቱ ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስታወሻን መስጠት አሰፈላጊ ልሆን ይችላል። የሚሰጣቸውም ማስታወሻ ተማሪዎቹን የተማሩበትን አጠቃላይ ሁኔታ በማሳጠር የሚገልፁ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም ተማሪዎች፣ ከተማሪው መማሪያ መፃፍ እና ሌሎች መጽሐፎች ማስታወሻ እንዲወስዱ ዘዴዎችን ማስተማር ጥሩ ነው።

## ተከታታይ ግምገማ

በመማር ማሰተማር ሂደት ውስጥ፣ መምህሩ ስለተማሪ ብቃት መረጃ ለማግኘት ተከታታይ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ይኖርበታል። እንዲሁም ቀን በቀን የተማሪዎቹን ተግባር መከታተልና በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ችግር

ያለባቸውን ተማሪዎችን መለየት አለባቸው። መምህራን የተማሪዎቹን ችግሮች ካወቁ በኋላ ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለመወሰን የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።እንዲሁም

- እንዴት ማስተማር እንደሚቻል፣
- እንዴት መጠየቅ እንደሚቻል፣
- ምን እንደሚያስተምሩ
- ተማሪዎች እንዴት መማር እንዳለባቸው መከታተል ይሆናል።

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ይህ ክፍል ልታዩና ሊዳሰሱ የሚችሉትን ወይም ሌሎች ለመማር ማስተማር የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ያካትታል። እነዚህ አጋዥ ቁሳቁሶች የተማሪዎችን የመማር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ሞዴሎች፣ ሥዕሎች፣ የፊዴል ገበታዎችን፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ፖስተሮች እና የመሳሰሉ አጋዥ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ጥቅም ላይ ማዋል ነው።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ሥር የተለያዪ የምርጫ ጥያቄዎችና ማብራርያ የሚፈልጉ ጥያቄዎች መልሶቻቸው በግልጽ ቀርበዋል። እነዚህም ጥያቄዎች ተማሪዎች በተረጋጋና በጥልቀት እንዲያስቡ የሚያበረታቱ ናቸው።

## የትምህርት ዕቅድ

በዚህ የመምህሩ መመሪያ መጨረሻ ላይ አንድ የትምህርት ዕቅድ ናሙና ይገኛል። ስለዚህ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የራስችሁን ጥሩ የትምህርት ዕቅድ

ማዘጋጀት ያስፈልጋል።ጥሩ የትምህርት ዕቅድ ደግሞ መግቢያ፣የትምህርት አቀራረብ ዘዴን፣ ማጠናከሪያና ግምገማን ያካትታል ።

**መግቢያ**፡ ይህ ክፍል መምህሩ የወቅቱን ርዕሰ ጉዳይ ካለፈው ጋር የሚያገናኝበት የዕቅድ አካል ነው።

1. **የትምህርት አቀራረብ ዘዴ፡** መምህሩ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ አጭር ማብራሪያ ለተማሪዎቹ የሚሰጥበትና ቀደም ሲል የተከናወኑ ተግባራትን ተማሪዎቹ እንዲተገበሩና በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ የሚያደርግበትና የዕቅዱ አካል ነው።
2. **ማጠናከሪያ፡** መምህሩ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ገምግሞ የዕለቱን ትምህርት በማጠናከር የተማሪዎቹን ሃሳብ የሚያሰባስብበት የዕቅድ አካል ነው።
3. **ግምገማ፡**ይህ ክፍል በመጨረሻ መምህሩ ተማሪዎቹ ቢያንስ ሊያገኙት የሚገባቸውን የትምህርት ክህሎቶች ላይ መድረሳቸውን የሚያረጋግጥበት ነው።

# ምዕራፍ 1፡ ራሰን መሆንን ማጎልበት

(የተመደበው ጊዜ፡20 ሰዓት)

በሦስተኛ ክፍል ትምህርት ተማሪዎች የስነምግባርና በራስ የመተማመን ጽንሰ-ሀሳቦችንና እራሳቸውን እንዲሁም ሌሎችን ለመረዳት የሚያስችሉ መሰረታዊ ነገሮችን እንደተማሩና ይህም በራስ መተማመንን ለማዳበርና ለራሳቸው አዎንታዊ አመለካከትን ለማዳበር ያለመ እንደነበር ያሰታውሱ። በዚህ ክፍል ደግሞ ስለራስ መሆንን ምንነት፣ የራስ መሆንን አስፈላጊነት፣ ለራስ ከፍ ያለ ግምትን የማዳበር ችሎታዎችንና ለራስ ከፍ ያለ ግምት አለመስጠት ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶችንም እንዲማሩ መገንዘብ አሰፈላጊ ነው።

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች ፡**

- የራስ መሆንን ትርጉም መግለጽ፣
- የራስ መሆንን አስፈላጊነት መግለጽ፣
- ራስ መሆንን የሚያጠናከሩ ዘዴዎችን መለየት፣
- ራስ የመሆንን ባህሪያት ማሳየት፣
- ችግር ፍቺ ክህሎቶችን ማዳበር፣
- ራስ ያለመሆን የሚያስከትለውን ውጤት መለየት።

## 1.1. ራስን መሆን

ይህንን ትምህርት በሚከተለው መልኩ ማስተማር አስፈላጊና ወሳኝ ነው።

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ራስን የመሆንን ምንነት ይገልፃሉ።
- ለራስ ከፍ ያለ ግምትን ለመጨመር የሚረዱ ዘዴዎችን ይዘረዝራሉ።

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ለራስ ከፍ ያለ ግምት መስጠትንና እንዴት በራስ የመተማመን ስሜትን ማዳበር እንደሚችሉ ይማራሉ። በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አጋዥ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የታዋቂ ግለሰቦችንና የቡድን ፎቶግራፎችን ወይም ስዕሎችን መጠቀም ይችላሉ።

**የማስተማር ዘዴ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የጉዳይ ጥናቶችን፣ የቡድን ውይይቶችንና ትግበራዎችን ይጠቀሙ።

**መግቢያ፡** አዲሱን የትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ መጻፍ፡ ያለፈውን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦችን በማሰታወስ ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ተማሪዎቹን ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

**የትምህርት አቅርቦት፡** የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦችን ማቅረብ ወሳኝ ነው። ራስን መሆን አንድ ሰው ለራሱ የሚሰጠውን ቦታ ያሳያል። ይህም ራስን በማክበር ይጀምራል ። አንድ ሰው እራሱን ገምግሞና ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ያለውን ችሎታ የሚያሳየው ለራሱ ከፍ ያለ ግምት መስጠቱን ያሳያል።

ስለዚህ በራሱ የሚተማመን ሰው የራሱን ችሎታ የሚያውቅና ከሌሎች ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ሰው ነው። ራስን መሆን አንድ ሰው የተሰጠውን ተግባር በታማኝነትና በብቃት ማጠናቀቅ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ተማሪ የቤት ስራን፣ የክፍል ስራንና፣ ፈተና ራሱን ችሎ ከሰራ በራሱ የሚተማመን ተማሪ ነው። በዚህም መሰረት በመማሪያ መጽሐፉ የጉዳይ ጥናት ውስጥ የተጠቀሰው ቤካ የተባለው ተማሪ በራስ መተማመንን አስመልክቶ በፈተና ወቅት የሚያሳየው ብቃት ተገልጿል። ይህም

የተማሪውን የቤተሰብ ታሪክንና በትምህርት ቤት ያዳበረውን ልምድ ያጠቃልላል። በክፍል የመገኘትንና የትምህርት ስኬት፣ ለራስ ክብር መስጠትን ፣ መጥፎ ባህሪን ማስወገድን ከተማሪው ራስን መገምገም ቁልፍ ነጥቦች ጋር የተያያዘ ነው።

**ማጠናከሪያ** ፡ በዚህ ደረጃ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ማጠቃለል ተገቢ ነው። ይህም ስለ ተማሪ ቤካ ለራሱ ያለውን ግምትና ራሱን የመገምገምና የክፍል ትምህርትን ለመከታተል ያለው ቁርጠኝነት፣የቤት ሥራ መሥራት፣ ጠንክሮ ማጥናትና በፈተና ወቅት በመረጋጋት፣ በፈተና ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ስኬትን ማሳየት፣ በራሱ ችሎታ ላይ ያለውን እምነትንና በራስ በመተማመን መማር መቻሉን በማስገንዘብ ማጠቃለል ይገባለ።

**ግምገማ** ፡ ጥያቄዎችን በመይጠየቅ እና በመልሶቻቸው ላይ አስተያየት መስጠት። ከትምህርቱ አቀራረብ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

→ ተማር ቤካ በፈተና ወቅት ደስተኛና የተረጋጋ መሆን የቻለው ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ። ቤካ እራሱን የሚያከብር፣ንቁና ጠንካራ፣ ሁል ጊዜ ክፍል ውስጥ የሚገኝ፣ የቤት ስራንና የክፍል ስራዎችን በሰዓቱ የመስራት ችሎታውን ያዳበረ ተማሪ መሆኑን መልስ መስጠት መቻላቸውን ማረጋግጥ። ቤካ ሁል ጊዜ ለራሱ ትምህርት ሃላፊነት እንደሚወስድና ደስተኛ እና የተረጋጋ እንዲሆን በራስ የመተማመን መንፈስ እንዳዳበረ በመናገር መልሶቻቸውን በማረጋገጥ ተማሪዎቹን አበረታቷቸው።

→ በፈተና ወቅት ቤካ ራሱን እንዴት ይመለከታል? የሚለውን ጥያቄ ይጠይቁና ተማሪዎች በቡድን እንዲወያይበት ያድርጉ። ቤካ የትምህርት ስራዎችን መስራት የሚችል እና በራሱ የሚኮራ ተማሪ መሆኑን ተማሪዎቹ መናገር

መቻላተቸውንና የተማሪዎች ፈተና መስረቅንም ሆነ ማጭበርበርን እንደሚያወግዝ እንዲያስታውሱ ማበረታታት ያስፈልጋል።

**የተግባር 1.1 ጥያቄዎች እና መልሶች**

1. ከዚህ አጭር የጉዳይ ጥናት ምን ተማርክ/ሽ ?
2. ጠንካራ ተማሪ እንደሆንክ/ሽ ታስባለህ/ብያለሽ?
3. በምን ዓይነትሥራዎች ቤተሰብህን/ሽን ታግዛለህ/ዢያለሽ?

ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ተማሪዎቹ የጥያቄውን መልስ በቃል እንዲመልሱና ስለራሳቸው የሚያውቁትንና የሚያስቡበትን እንዲናገሩ እርዷቸው።መልሳቸውም የትምህርቱን ይዘት ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ለማወቅ ይረዳል። እንዲሁም ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገመግሙና ለሚቀጥለው የትምህርት ይዘት እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል።

**1.2.ራስን የመሆን ባህሪያት**

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ራስን የመሆን ባህሪያትን ይዘርዘራሉ፣
- በራስ የመተማመን ባህሪያትን ያሳያሉ።

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** ተማሪዎች የራስ መሆንን ጽንሰ-ሃሳብ ግንዛቤ አግኝተዋል፡ በዚህ ትምህርት ይዘት ደግሞ ራስን የመሆን ባህሪያትን ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የተለያዩ የመማር ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ማስተማር።

**የማስተማርያ ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችንና ትግበራዎችን መጠቀም።

**መግቢያ፡** አዲሱን የትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ መጻፍና ያለፈውን ትምህርት ዋና ዋና ሀሳቦችና ነጥቦችን በማሳታወስ ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ማሳወቅ ።

**የትምህርት አቅርቦት፡**ማብራሪያ ከመሰጠቱ በፊት ራስን የመሆን ባህሪያት ምንድን ናቸው?የሚለውን የግንዛቤ ጥያቄ በመጠየቅ ማስተማር መጀምር።

**የጥያቄ መመሪያዎች፡-**የግንዛቤ ጥያቄዎች በቃል የሚጠየቁና ተማሪዎች ራሳቸው የመሆንን ባህሪያት የሚያውቁትን ያህል በማብራራት ምላሽ እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል። መልሶቻቸው ካለፈው ትምህርት የተማሩትንና ለአዲስ ርዕስ እየተዘጋጁ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ይረዷቸዋል። በዚህ መሠረት ስለ ቢፍቱ እና ጫላ የጉዳይ ጥናት ላይ ተማሪዎች በመወያየት ራስን የመሆን ባህሪያትን ራስን መግዛት፣ በራስ መተማመንና ራስን መቻል ባህሪያትን እንዲለዩ ጠይቋቸው።

**ማጠናከሪያ ፡** ትረካውን በመጠቀም ተማሪዎች ራሳቸውን የመሆንና ራስን መሆንን ወይም በራስ መተማመንን ሊጎዱ የሚችሉ ባህሪያትን ለተማሪዎች በአጭሩ ያብራሩ።

**ግምገማ፡** ከማጠቃለያ ገለጻ በኋላ በተግባር 1.2 ስር ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ፈትሻቸው፡-

**ተግባር 1.2 መልስ**

1. ተማሪ ቢፍቱ ከሰዎች ጋር መልከም ግንኙነት በመመሰረት ራስን የመግዛት ልምድ በማዳበር ትታወቃለች። በሌላ በኩል ተማሪ ጫላ በተለያዩ ልምዶችና ክህሎቶች የሚታወቅና በራስ በመተማመን ስሜትና ራሱን በመቻል መስራት ይታወቃል።ስለዚህ ቢፍቱ እና ጫላ ተመሳሳይ ልምድ የላቸውም።
2. ጫላ ጠንካራና ውጤታማ ተማሪ መሆኑና ችግሮችን ተቋቁሞ አላማውን ማሳካቱ ነው።

**ሀ. በራስ መኩራት**

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡**ተማሪዎች በራስ መኩራት ምንነት በጥልቀት ይማራሉ። በራስ መተማመን ሰዎች በሌሎች ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ ራሳቸውን ችለው አንድን ስራ ወይንም ተግባር በመስራት የራሳቸውን ችግሮች በራሳቸው መፍታት መቻል ማለት ነው። በራስ መተማመን ተማሪው ለራሱ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጥበትና በእችላለሁ መንፈስ ስራውን በተሳካ ሁኔታ የሚያጠናቅቅበት ነው ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የተለያዩ የመማር ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ማስተማር።

**የማስተማርያ ዘዴዎች፡** አሳታፍ የመማር ማስተማር ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎች በቡድን ስራ በራስ በመተማመን ጽንሰ-ሀሳብ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ።

**መግቢያ**፡ ያለፈውን የትምህርት ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወስ የዕለቱን የትምህርት ይዘት ማስተዋወቅና ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን ማሳወቅ።

**የትምህርት አቅርቦት፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ያለውን በመጠየቅ ተማሪዎች ከተማሩት ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ ይጠበቃል። ለምሳሌ ራስን መቻል ምንድን ነው? ጥገኝነት ወይም ራስን አለመቻል ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በቃል በመጠየቅ እንዲያብራሩ አበረታቷቸው።

ራስን መቻል ራስን ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ ራሱን የሚችል ሰው የሌሎችን ድጋፍ ሳይጠይቅ የራሱን ችግሮች መፍታት እንዳለበት ያምናል። ጥገኝነት ደግሞ አንድን ተግባር ለመፈጸም ብዙ ጊዜ የሌላ ሰው ድጋፍ የሚፈልግ ሰው ነው።

**ማጠናከሪያ ፡ ስለ ጫልቱ የጉዳይ ጥናት**

ከጫልቱ ልምድ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ነጥቦች ለምሳሌ ከጓደኞቿ ጋር በመልካም ግንኙነት ላይ የተመሰረተ አብሮ የመኖር፣ ጠንክሮ የማጥናት፣ በፈተና ጥሩ ውጤት በራስ ማስመዘገብ ፣ በራስ የመተማመን ፣ ጊዜዋን በአግባቡ የመጠቀም ፣ መረጋጋትና ከሌሎች ጋር ያላት ጥሩ ግንኙነት የትምህርቱ ይዘት ማጠናከርያ ቁልፍ ነጥቦች ናቸው።

***ግምገማ*** ፡ ከማጠቃለያ ገለጻ በኋላ በተግባር 1.3 ላይ ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ ገምግሙ።

**የተግባር 1.3 መልሶች**

1ኛ. አዎ ! ጫልቱ በችሎታዋ ትተማመናለች ራሷንም ችላ ትምህርቷን ትማራለች።

2ኛ፡ አዎ! በራሱ የሚተማመን ሰው በብቃት ያምናል። በራስ በመተማመን ትምህርቱን የሚማር ተማሪ ችግር ወይም ከአቅሙ በላይ የሆነ ነገር ሲያጋጥመው ብቻ የሌላን ሰው ምክርና ድጋፍ የሚጠይቅ ነው።

3ኛ.ጫልቱ በትምህርቷ ላይ ችግር ሲያጋጥማት የሌሎችን እርዳታ ትጠይቃለች። ከአቅሟ በላይ ካልሆነ በስተቀር ጥገኛ አይደለችም።

4ኛ. ራስን በመቻል የሚገኙ ጥቅሞች፣ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ተማሪዎች በተሳካ ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ያስችላቸዋል፣ ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ውስጥ በራስ የመተማመንና ራስን የመሆንን ባህሪይን ያዳብራሉ። በተጨማርም ራስ መግዛትን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል።

**ለ. በራስ መተማመን**

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ይዘት በራስ የመተማመንን ጽንሰ-ሐሳብ ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ ስዕሎችን በማሳየት ማስተማር።

**የማስተማሪያ ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን በመጠቀም።

**መግቢያ፡**የዕለቱን የትምህርት ይዘት በማስተዋወቅ ያለፈውን የትምህርት ዋና ዋና ነጥቦችን ማሰታወስና ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን በመግለጽ ።

**የትምህርት አቅርቦት፡** በራስ መተማመን ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ በቃል በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲያብራሩ መጠየቅ።ተማሪዎች ስለ በራስ የመተማመንን ጽንሰ ሃሳብ የሚያውቁትን ያህል በማብራራት ምላሽ እንዲሰጡ አግዙአቸው። በራስ መተማመን በማንኛውም ተግባር ውስጥ ስኬታማ ሆኖ መገኘት ነው። አንድን ተግባር በራስ መተማመን ለማከናወን በቂ ችሎታ እንዳለን የሚያሳይ ነው። ይህም የራሱን ብቃቶች በማወቅና በትጋት የተሞላ ተነሳሽነት ካለው ሰው የሚመነጭ ነው። በራሱ የሚተማመን ተማሪ በክፍል ውስጥ በጥሩ ስሜት ይሳተፋል/ትሳተፋለች።እንዲሁም በቤት ስራና በቡድን ስራ ላይ ጠንክሮ ይሰራል/ትሰራለች።ስለዚህ ተማሪዎች የየራሳቸውን የጥናት ዕቅድ በማውጣት እንደሚማሩ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። በራስ መተማመን አስመልክቶ "ከደፋር ሰው ዘፈን ያምራል" የሚል አባባል አለ። ይህም ምን እንደሆነም ተማሪዎቹን ጠይቋቸው።

**ማጠናከሪያ፡** በራስ የመተማመን ባህሪይ በትምህርት ላይ ያለውን ተጽእኖ ተማሪዎች እንዲወያዩበት አድርጉ ።-ስለ ተማሪ አበበች እና ወንድሟ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን የጉዳይ ጥናት ላይ በማተኮር የተማሪዎቹን ግንዛቤ ማጠናከር። የአበበች የመማር ልምድና የወንድሟን ምክር የመቀበል፣ በራስ የመተማመን ስሜቷን ለማሻሻል ያደረገችው ለውጥና የወንድሟን ምክር በመቀበል በትምህርቷ ላይ ያሳየችው መሻሻል የዚህ ትምህርት ዋና ዋና

ነጥቦች ናቸው። ስለዚህ ተማሪዎች የጉዳይ ጥናቱን የተረዱትን ያህል እንዲያብራሩ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

**ግምገማ**፡ ከማጠቃለያ ገለጻ በኋላ በተግባር 1.4 ላይ ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ ገምግሙ ።

## የተግባር 1.4 መልሶች

1.መምህራን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች ስለራሳቸው እንዲያስቡ ማበረታታት። እያንዳንዱ ተማሪ ሁሉንም ጥያቄዎች በተናጥል እና በቡድን መሞከርና ለክፍል ጓደኞቹ ማቅረብ ይጠበቅበታል። የተረዱበት መንገድ የተለያዩ ሊሆን ሰለሚችል ሁሉም ተማሪዎች መልሱን እንዲያብራሩ ማድርግ ከዚህ አንጻፃር በራስ ያለመተማመን ምልክቶችና የግል ባህሪያት:-

ሀ) ዓይንአፋርነት ለ) ፍርሃት ሐ) መጨነቅ ናቸው። በራስ የመተማመን ደግሞ ሰዎች ከሌሎች ጋር እንዲግባቡ፣ ችግሮችን እንዲፈቱና እንዲያሸንፉ እንዲሁም በትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። ስለሆነም ተማሪዎች ክፍል ገብተው የቤት ስራቸውንና የቡድን ሥራን በሰዓቱ እንዲያጠናቅቁና በዕቅድ እንዲያጠኑ ይረዳል፡፡

3. ከወንድሟ ምክርና ድጋፍ በማግኘት በራስ የመተማመን ስሜቷን አጠናክራለች።

4. ተማሪዎች በራስ በመተማመን ስራቸውን እንዲሰሩ ይረዳል።

5. በራስ የመተማመንን ባህሪይን ለማሻሻልና በሃላፊነት ስሜት በመስራት፤ ከቤተሰብ፣ ከጓደኞችና ከመምህራኖች ምክር መቀበል።

## ሐ. ራስን መግዛት

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** ለተማሪዎች  በራስ የመግዛት ምንነት ላይ በቂ ግንዛቤ መስጠት።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የታዋቂ ግለሰቦችን፣ የቡድን ፎቶግራፎችንና ገላጭ የሆኑ ስዕሎችን  በጠቀም  ማስተማር ።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን በመጠቀም።

**መግቢያ፡** ያለፈውን የትምህርቱን ይዘት ዋና ዋና ነጥቦችን ማሰታወሰና የዕለቱን ርዕስ  ማስተዋወቅ። ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ  የመማር ብቃቶችን መግለጽ ።

**የትምህርት አቅርቦት፡** ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ምሳሌያዊ አነጋገርን አንብበው አስተያየት እንዲስጡ በማድረግ መጀመር። እያንዳንዱ ተማሪ ለምሳሌያዊ አነጋገር ምላሽ በመስጠትና ስሜታቸውን እንዲያጸባረቁ በማድርግ  ምሳሌያዊ አነጋገሮቹን መረዳት አለባቸው።

**ማጠናከሪያ፡** ስለ ጫልቱ የጉዳይ ጥናት፣ ራስን የመግዛት ጽንሰ ሃሳብ ለተማሪዎች በአጭሩ አብራሩ። ራስን መግዛት ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን ከማድረግ መቆጠብ ነው። ራስን መግዛት ሌሎችን ሊጎዱ ከሚችሉ ድርጊቶች መቆጠብና አለማድርግ ነው፡፡ ለምሳሌ ከጓደኞችህ ጋር ሲትጫወት በንግግሮችህ እንዳትጎዱዋቸው ራስህን መቆጣጠር አለብህ/ሽ። አንዳንድ ሰዎች ራስቸውን መግዛት ይጎላቸዋል፡፡ ራስን መግዛት አስፈላጊና

በማንኛውም ማህበራዊ ህይወት ውስጥም መኖር  እንደሚገባ ለተማሪዎች አጽንኦት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ግምገማ** ፡ ከማጠቃለያ ገለጻ በኋላ በተግባር 1.5 ላይ ያሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎቹን የግንዛቤ ደረጃ ገምግሙ ፡፡

የተግባር 1.5 መልስ

መምህር፣ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን የተግባር 1.5 ጥያቄዎችን እያንዳንዳቸውን ተማሪዎች አስበውበት እንዲመልሱ አበረታቷቸው፡፡ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በተናጥል እና በቡድን ሞክረው  መልሱን  ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ፡፡

1. ማንነቱን ከማያውቁት ሰው ጋር አብሮ መሄድ ለችግር ልዳርግ  እንደሚችል ያስረዳል፡፡
2. በጓደኞቻቸሁ በኩል የሚደረጉ  አላስፈላጊ ግፊቶችና ጫናዎችን  እንዲሁም ትኩረትን የሚስቡ ነገሮችን በማስወገድ፤ግቦችን በማወቅ፤ ምን ምን ማድረግ እንዳሌባችሁና እንደሌለባችሁ መወሰንና  ጓደኛን  መለየት፡፡
3. ተማሪዎች መልሱን አዎ ወይም አይደለም ሊሉ ስለሚችሉ አዎ ወይም አይደለም ያሉበትን ምክንያት  ለምን እንደሆነ በትክክል እንዲያብራሩ ጠይቋቸው፡፡ በመጨረሻም  ስዎች ከመጥፎ ተማሪዎች ራሳቸውን የመቆጣጠር  ችሎታውን እንዲያዳብሩ ማስረዳት፡፡

## 1.3. በራስ መኩራትን ማዳበር የሚቻልባቸው መንገዶች

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- በራስ የመተማመን ባህሪያትን እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ ትገልጻለህ/ሽ
- በራስ የመተማመን ባህሪያትን ታሳያለህ/ሽ፣

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርት ርዕስ ውስጥ ተማሪዎች ራስን የመሆንን ወይም በራስ የመኩራት ባህሪያትን እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የታዋቂ ግለሰቦችን፣ የቡድን ፎቶግራፎችንና ገላጭ የሆኑ ስዕሎችን በጠቀም ማስተማር ።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን መጠቀም።

**መግቢያ፡**ያለፈውን የትምህርት ይዘት ዋና ዋና ነጥቦችን ማሰታወስና የዕለቱን የትምህርት ርዕስ ማስተዋወቅ።ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን መግለጽ ።

**የትምህርት አቅርቦት፡** አንድን ሰው ስለራሱ ያለውን ግምት ለማጠናከር የሚረዱ ነገሮችን እንዲዘረዝሩ ተማሪዎችን ጠይቋቸው። በራስ መተማመን በተማሪዎች ትምህርት ላይ ያለውን ሚና ለማሻሻል እንዴት እንደሚረዱ ማብራራት ወሳኝ ነው። በዚህ መሠረት አንድ ሰው ለራሱ ያለውን ግምት ለማጠናከር የሚረዱ ድርጊቶች ተዘርዝረዋል። ስለዚህ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ መወያየት አስፈላጊ ይሆናል ።

- የራስን ችሎታ መረዳትና ማድነቅ;
- በፈገግታና አይን ለአይን በመተያየት በራስ መተማመን መንጋገር;
- በእችላሁ ስሜት መሥራት;
- መልካም ስነ ምግባር ካላቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር
- ማንነትህን የሚያከብሩ ጓደኞችን ማፍራት ናቸው።

**ማጠናከሪያ፡** በዚህ ደረጃ፣ ትምህርቱን መገምገም ፤ ማጠቃለልና ማጠናከር።

**ግምገማ፡** ከማጠቃለያ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ።

1. አንድ ሰው ለራሱ ያለውን ግምት ለማጠናከር የሚረዱ በህሪያት ላይ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግና ተማሪዎችን በመምራት በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ ከተወያዩና ከተለማመዱ በኋላ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ አጭር ማብራሪያ ለተማሪዎች መስጠት።

ሀ. አንድ ሰው ችሎታውን አውቆ መጠቀም

ለ. ራስን በመተማመን ከሰዎች ጋር መግባባት

ሐ. ራስን የመቻል ስሜት ማዳበር

መ. ጥሩ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር መገናኘትና በራስ ከሚተማመኑ ጓደኞች ጋር መወዳጀት የራስን ግምት ለማሻሻል ይረዳል።

## 1.4. በራስ የመኩራት ጥቅሞች

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ራስ የመሆንን አስፈላጊነት ያደንቃሉ።

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** ተማሪዎች ለራስ ከፍ ያለ ግምት በሚሰጡ ጥቅሞች ላይ እንዲያተክሩ ፣ በተለይም ራስ መሆን የተማሪዎችን ህይወት ለማሻሻል ባለው ጠቀሜታ ላይ ያተኩራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን መጠቀም።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን በመጠቀም።

**መግቢያ፡** ያለፈውን የትምህርት ይዘት ዋና ዋና ነጥቦችን በማሰታወስ እና የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን መለየት።**የትምህርት አቅርቦት፡** እያንዳንዱን ተማሪ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲያስቡበትና ከዚያም ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲሰጡ አበረታቷቸው። ተማሪዎች ሁለቱንም ጥያቄዎች በተናጥልና በቡድን ምላሻቸውን ለክፍሉ ማቅረብ አለባቸው።

የጥያቄው መልስ

1. አዎ፤ በራስ መተማመነ ሕይወቴን ለማሻሻል ያስችለኛል። ራሴን ችዬ አንድን ስራ እንዲፈጽምና በራሴ እምነት እንዲኖረኝ ያደርገኛል።ለራስ

ማስብና አዎንታዊ ስሜቶች መኖር፡በራስ የመተማመንና ራስን የማክበርን ስሜትን ያዳብራል።

2. ራስን መሆን በትምህርት ስኬት ውስጥ ያለው ሚና፡ በራስ የመተማመንን ስሜትን ለማዳበርና ለራስ የሚገባ ክብር ለመስጠት፤ በጥንካሬና ድክመቶቻችን እንዲናምንና –በአዎንታዊ መልኩ እንድናስብ ያስችለናል ።

**ማጠናከሪያ፡** ራስን የመሆን አስፈላጊነትን ለተማሪዎች በአጭሩ አብራሩ። ለራስ የሚገባ ክብር በመስጠት ተማሪዎች የአስተሳሰብ ችሎታቸውን፣ አዎንታዊ ስሜታቸውንና ለራሳቸው ያላቸውን ግምት እንዲያውቁ ወይም እንዲቀበሉ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች በራሳቸው የመወሰንን፣በሥራቸው እንዲኮሩና በሕይወታቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ ያግዛቸዋል።በራስ የመተማመን ስሜት ባላቸው ተማሪዎች ውስጥ የመማር ተነሳሽነትን ይጨምራል።

**ግምገማ**፡ ከዚህ ትምህርት አቀራረብ በኋላ የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ። ይህም ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች ላይ መድረሳቸውን በማረጋገጥ የሚከተለውን ጥያቄ መጠየቅ አስፈላጊነው።

በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ስለ ራስን መሆንን አስፈላጊነት ተማሪዎችን የቃል ጥያቄ መጠየቅ። በጥያቄው ላይ ከተወያዩ በኋላ የተወያዩበትን እንዲያቀርቡ ተማሪዎቹን አበረታቷቸው።

**መልስ፡** ራስን መሆን የሚያስፈልገው ሰዎች አዎንታዊ ሀሳቦችንና ጠንካራ ስሜቶችን እንዲያገኙና እንዲያጎለብቱ እንዲሁም እንዲያውቁና እንዲከበሩ ለራሳቸው የሚገባ ክብር እንዲስጡ ይረዳቸዋል።

## 1.5. ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ተግዳሮቶችን መቋቋም የሚያስችሉ ችሎታዎችን ማዳበር
- ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ ማሳይት

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርት ተማሪዎች ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ እንዲያዳብሩ ይጠበቃል።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን መጠቀም።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣ የሚና ጨዋታዎች፤ የቡድን ውይይቶችን፣ ጥያቄዎችንና መልሶችን በመጠቀም።

**መግቢያ፡** ያለፈውን የትምህርት ይዘት ዋና ዋና ነጥቦችን በማሰታወስ እና የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን መለየት።

**የትምህርት አቅርቦት፡** እያንዳንዱን ተማሪ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲያስቡበትና ከዚያም ለጥያቄዎቹ መልስ እንዲሰጡ አበረታቷቸው። ተማሪዎች ሁለቱንም ጥያቄዎች በተናጥልና በቡድን ምላሻቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀመር።

1. ችግር ለአንተ/ለአንቺ ምንድነው?

2. በህይወታችሁ ውስጥ የሚያጋጥሟችሁን ችግሮች እንዴት ትቋቋማላችሁ?

ለእያንዳንዱ ተማሪ ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ እንዲያስቡበት አበረታታቸው። ተማሪዎቹ ሁለቱንም ጥያቄዎች በተናጥል እና በቡድን እንዲመልሱና ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አበረታታቸው።

**የጥያቄዎቹ መልስ**

1.ችግሮች ከአቅማችን በላይ የሆኑና ሊንቋቋማቸው የማንችላቸው ናቸው። ለመተግበር አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ለምሳሌ ሃሳቦች፣ ስልቶች እና የሌሎችን ድጋፍ ወይም ትብብር የሚያስፈልጉን ሊሆኑ ይችላሉ።

2. አንዳንድ ሰዎች በልቤ ሙሉነት ችግሮችን ሲያሸንፉ ሌሎች ደግሞ በችግር ይሸነፋሉ። ይሁን እንጅ ችግር አንዳንድ ጊዜ ዕድልም ሊሆኑም ይችላሉ። ምክንያቱም ችግር በዙሪያችን ያለውን እውነታ ለመመርመርና ለማወቅ ይረዳናል። በአግባቡ ጥቅም ላይ ካዋልን እያንዳንዱ ችግር መፍትሄ ይኖረዋል። ይህም ችግሮችን ለማሸነፍ የሚያስችል አቅም እንድናዳብር ያስችለናል።

**ማጠናከሪያ፡** ችግሮችን የመቋቋምን ችሎታን አስመልክቶ ማብራሪያ መስጠት። የሰው ልጅ ህይወቱ በፈተና የተሞላ ሲሆን ለዕድገት ዕድሎች እንደሚዳርጉ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህም ሰው ችግሩን ለመቋቋም ጠንክሮ እንዲሠራ ያደርገዋል። እንዲሁም ተማሪዎች በፈተና እንዳይወድቁ ያለመፍራት ጠንክረው እንዲሰሩና ውጤታቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋቸዋል።ይህ ማለት ተማሪ በክፍል ውስጥ የመውደቅን ችግር ለመቋቋም የበለጠ ይሰራል ማለት ነው። ተማሪዎች ችግሮችን ለመቋቋም ችሎታ አላቸው። ስለዚህ የግል ችግሮቻቸውን የሚፈቱበትን መንገድ በተሻለ ሁነታ ማሳየት ያስፈልጋል።

ተማሪዎች ሁኔታቸውን፣ ሀብቶቻቸውንና ችሎታቸውን በመዳሰስ እርምጃ እንዲወስዱና እንዲተገብሩ በመምራት የችግር አፈታት ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ መርዳት ወሳኝ ነው። **ግምገማ** ፡ ከአጠቃላይ ገለጻ በኋላ የሚከተሉትን የተግባር 1.6 ጥያቄዎች በመጠየቅ የተማሪዎቹን የመረዳት ሁነታ ገምግሟቸው፡-

## የተግባር 1.6 መልሶቻቸው

ተማሪዎች ችግሮችን እንዲቋቋሙ የሚረዷቸውን ክህሎቶች እንዲወያዩባቸው ማድረግ።በመጨረሻም ችግሮችን የመቋቋም ችሎታቸውን የቃል ጥያቄዎችን በመጠየቅ በጥያቄው ላይ ከተወያዩ በኋላ አጭር አስተያየትና ትክክለኛውን መልስ ለተማሪዎች መስጠት ያስፈልጋል።

1. ውድድሩን ያቋረጡ ኤሊዎች በራስ የመተማመን ባህሪ የላቸውም።
2. አዎ፣ ምክንያቱም የውድድሩ አሸናፍ ኤሊ ጆሮው የሚሰማ ቢሆን ኖሮ እንደሌሎቹ ተስፋ ቆርጦ ይመለስ ነበር ነገር ግን ያለመስማቱ ውድድሩን እንዲያሸንፍ ጥሩ ዕድል ሰጠው።ስለዚህ ችግሮች ወደ ጥሩ ዕድል የሚቀየሩበት አጋጣምዎች መኖሩን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

## 1.6. ራስን ያለመሆን ውጤቶች

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ራስን ያለመሆን የሚያስከትለውን ተጽኖ መግለጽ፤
- በራስ መተማመን የለላቸውን ሰዎች ባህሪያትን መለየት።

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርት ተማሪዎች በራስ የመተማመን እጦትን ወይም በራስ የመተማመን እጦት የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የፊዴል ገበታዎችንና ስዕሎችን በመጠቀም ማስተማር።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፤ የቡድን ውይይቶችንና ቃለ-መጠይቆችን መጠቀም።

መግቢያ፡ ያለፈውን ትምህርት ይዘት ዋና ዋና ነጥቦችን በማሰታወስና የዕለቱን ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን መግለጽ ።

**የትምህርት አቅርቦት፡** በራሱ የማይተማመን ሰው ምን ምን ማድረግ እንደማይችል ወይም ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ባህሪያት ምን እንደሆኑ የግንዛቤ ጥያቄዎችን በቃል በመጠየቅ መጀምርና ዋና ዋና ነጥቦቹን በማሳጠር መግለጽ።

በመጀመሪያ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲያስቡ በማበረታታት፣ በመቀጠል ተማሪዎች ጥያቄውን በተናጠል እንዲሠሩ ፣ በግልና በቡድን ሆነው የሰሩትን መመልከት። በመጨረሻም ተማሪዎቹ መልሱን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ማብራራት።ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ በማጠናከሪያ ትምህርት ሥር ተዘርዝረዋል ።

ማጠናከሪያ፡- ለራስ ከፍ ያለ ግምት ማጣት ወይም ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ባህሪይ በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በአጭሩ መግለጽ፤ ለራሳቸው ዝቅተኛ ግምት ያላቸው ሰዎች የሚከተሉት ባህሪያት አሏቸው፡፡

- በራሳቸው ላይ እምነት ማጣት ወይንም በራስ የመተማመንን ስሜት ማጣት
- ራሳቸውን አቅመ ቢስ ወይም ራስን እንደ ተሸናፊ ማየት፤
- ስህተታቸውን ለመቀበል ወይም ይቅር ለማለት መቸገር፤
- ላለመሳሳት በፍርሃት ዝም ማለት፤
- ለትምህርት ፍላጎት ማጣት፤
- ማንኛውንም ነገር ራስን ችሎ መስራት አለመቻል ናቸው፡፡

**ግምገማ**፡- ከአጠቃላይ ገለጻ በኋላ የሚከተሉትን የተግባር 1.7 ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎቹን የመረዳት ደረጃ መገምገም፡፡

የተግባር 1.7 መልስ

1. ዝቅተኛ በራስ የመተማመን ባህሪይ ያላቸው ሰዎች የሚያሳዩት ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው፡፡እነዚህም በህይወታቸው የማይደሰቱ፤የመማር ፍላጎት

የሌላቸው ፤ብዙውን ጊዜ ለብቻቸው የሚያሳልፉ፤ትችትን የሚያበዙ፤ደፍሮ ከመስራት የሚፈሩ፤ለሥራ አለመነሳሳት ወይም ተነሳሽነት የሌላቸው፤ የቤት ሥራና የቡድን ሥራን ያለመሥራት፤ጠባቅነተንና የመሳስሉትን ባህሪያት ያሳያሉ።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥቄዎች መልሶች

### ክፍል አንድ፡-

1. እውነት 2. እውነት 3. ሐሰት

### ክፍል ሁለት፡-

1. መ 2. ሐ 3. ለ 4. ሀ

### ክፍል ሦስት፡-

1. ለ 2. ለ 3. መ 4. ለ 5. መ

# ምዕራፍ 2፡ ሰብአዊ መብቶች

(የተመደበው ጊዜ፡21 ሰዓት)

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች**፡-

- የሰብአዊ መብት መከበር አስፈላጊነትን መግለፅ፣
- በመብቶች እና ኃላፊነቶች መካከል ያለውን  ግንኙነት መለየት፣
- ሰብዓዊነትን ማክበር፣
- የህጻናት፤ የሴቶች እና አካል ጉዳተኞችን፣ መብቶች መግለጽ፣
- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ባህሪን ማሳየት።

## 2.1. ሰብአዊ መብቶች

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ሰብአዊ መብቶችን ይገልጻሉ
- የሰብአዊ መብቶችን ምሳሌዎችን ይናገራሉ።

**አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርትይዘት ውስጥ ተማሪዎች ስለ ሰብአዊ መብቶች ይማራሉ።ሰብአዊ መብት ለአንድ ሰው የተሰጠውና  በሌላ ሰው ወይም አካል ሊወሰድበት የማይገባው ነው። ይህም አንድ ሰው ምን ማድረግ እንደሚችልና ምን እንዳለው የሚያሳይ ነው።

ሰብአዊ መብቶች ለሰው ልጆች በሙሉ በጣም አስፈላጊ ናቸው። የሰዎች አብሮነት ባለበት ቦታ ሁሉ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በትምህርት ቤት እና

በስራ ቦታ ሁሉ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በይበልጥ ደግሞ በመንግስት እና በህዝብ መካከል ባለው ግንኙነት ይታያል። በመሆኑም ሰዎች ስለ ሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል። ሰብአዊ መብቶችን መረዳትና መተግበር ሰላምን፣ ፍትህንና የህብረተሰቡን የጋራ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ይረዳል።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡የሰብአዊ መብቶችን አከባበር የሚያሳዩ ምሥሎችን ወይም ሥዕላዊ መግላጫዎችን መጠቀም።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** ተማሪዎች በቡድን ሆነው ስለሰብአዊ መብቶች እንዲወያዩ ማድረግና የግንዛቤ ጥያቄዎችን፣የቡድን ውይይቶችንና ርፖርት ተጠቅሰዋል።

**መግቢያ**፡ ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት ከዕለቱን ትመህርት ርዕስ ጋር ማስተዋወቅ።

**የዕለቱን የትምህርት ይዘት ማቅረብ፡**

**የመቢያ ጥያቄ**

**ተግባር 2.1**

1. ሰብአዊ መብቶች ምንድናቸው?
2. ቢያንስ ሶስት የሰብአዊ መብቶች ምሳሌዎችን ተማሪዎች ይዘርዝሩ።

ይህ ጥያቄ የቃል ጥያቄ ነው። ሲጠይቁ ተማሪዎች በቃል ምላሽ መስጠትና ምሳሌዎችን መስጠት አለባቸው። ከዚያ በመልቸው ላይ በመመስረት ግብረ-መልስ መስጠት ይቻላል።

ሰብአዊ መብቶች ሁሉም ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ የሚኖረው መብት ነው ። እነዚህ ሰብዓዊ መብቶች ከተፈጥሮአዊ መብቶች ጽንሰ-ሀሳብ የተወሰዱ ናቸው። ሰብአዊ መብቶች የሚባሉት በሕይወት የመኖር መብት የነፃነት መብት፣ የእኩልነት መብት፣ በሰላም የመኖር መብት፣ ከባርነትና ሰቆቃ ነፃ የመሆን፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የመስራት መብት፣ የመማርና እና ንጹህ አከባቢ የመኖር መብቶችን ያጠቃልላል ።

## የተግባር መልስ

1. በሰላም የመኖር መብት፣ ምግብ የማግኘት መብት፣ የተለያዩ አገልግሎቶች ማለትም የውሃ፣ የመብራት፣ የመንገድ፣ ወዘተ የማግኘት መብት።

2. ንብረት የማፍራት መብት፤የመናገር መብት፤ መኖሪያ ቤት የማግኘት ናቸው።

## 7. ክለሳ

ስለ ሰብአዊ መብቶች ትርጓሜ እና ምንነት አጠር ያለ ማብራሪያ ይስጡ እነሱም፡-

- የሰብአዊ መብቶችን ጽንሰ-ሀሳብ ማብራራት፣
- የሰብአዊ መብቶችን ባህሪያት መግለጽና ምሳሌዎችን መስጠት።

ሰብአዊ መብቶች የሰው ልጆች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚኖራቸው መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች ናቸው። በትውልድ ስፍራ፣ በሃይማኖት፣ በኑሮ ሁኔታ እና በመሳሰሉት ሳይገደብ የሚተገበር ነው። እነዚህ መብቶችና ነጻነቶች የተሰጡት ለሰብአዊነት ክብር ብቻ ሲሆን በአጠቃላይ ሰብአዊ መብት ሲባል

ሁሉም ሰው ከአካላዊም ሆነ ስነ ልቦናዊ ጥቃት ነጻ የመሆን መብት አለው። ይህም ማለት ማንም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ እስካልተረጋገጠበት ጊዜ ድረስ እነዚህን መብቶች መከልከል የለበትም።

**ግምገማ፡** ጥያቄዎችን መጠየቅ እና ለተማሪዎች ግብረ-መልስ መስጠት።

የዕለቱ የትምህር ይዘት ከተጠናቀ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ

1. ሰብአዊ መብቶች ምንድናቸው?
2. የሰብአዊ መብቶች ባህሪያት ምንድናቸው?

**የተግባር ጥያቄዎች መልስ**

1. አንድ ሰው ምን ምን መብቶች አሉት?

2. ቢያንስ ሶስት የሰብአዊ መብቶች ምሳሌዎችን ዘርዝር።

**መልስ**

1. በህይወት የመኖር መብት ፤ የነፃነት መብት፣ የእኩልነት መብት፣ በሰላም የመኖር መብት፣ ከባርነትና ከሰቆቃ ነፃ የመሆን መብት ፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት፣ የመስራት መብት እና የመሳሰሉት ናቸው።

2. በህይወት የመኖር መብት የነፃነት መብት፣ የእኩልነት መብት፣ በሰላም የመኖር መብት፣ ከባርነትና ከሰቆቃ ነፃ የመሆን መብት ፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት፣ የመስራት መብት፣ የመማር እና ንጹህ አከባቢ የመኖር መብቶች ውስጥ ሦስቱን ብቻ መግለጽ ይችላሉ ።

**የተግባር 2.2 መልስ**

1. የሰብአዊ መብቶች ብቸኛው መስፈርት -----------------------------------ነው።

**መልስ፡- ሰብዓዊነት**

በዕለቱ የትምህርት ይዘት መጨረሻ ላይ ከላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ በማድረግ የተማሪዎቹ የዕለቱን ትምህርት ምን ያህክል እንደተረዱ ለመለየት ይረዳል። ተማሪዎች ራሳቸውን እንድገመግሙና ለቀጣዩ የትምህርት ርዕስ እንዲዘጋጁ ይረዳቸዋል።

## 2.2. የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት መዘርዘር፤
    - ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ዋጋ መስጠት።

**አጠቃላይ እይታ፡** ባለፈው ትምህርት ተማሪዎች ስለ ሰብአዊ መብቶች ምንነት ተምረዋል። በዚህ ትምህርት ደግሞ የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነትን ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነትን የሚያሳይ ቻርቶችን ወይም ምስሎችን መጠቀም።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን፤ የቡድን ውይይቶችንና ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ።

**መግቢያ**፡ ከዕለቱ ርዕስ ጋር በማስተዋወቅ ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

6. የለቱን ትምህርት ማቅረብ፡-

የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤

1. የሰብአዊ መብቶች መከበር ለህብረተሰቡ ምን አስተዋጽኦ አለው?

2. የሌሎችን መብት በማክበር እና ሌሎች መብታችንን እንዲያከብሩ በመጠበቅ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው?

3. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢም ሆነ በክፍል ውስጥ የሰብኣዊ መብቶች መከበርን አስፈላጊነት እንዲገልጹ ማድረግ

ከላይ ያሉትን የግንዛቤ ጥያቄዎች ተማሪዎች በንቃት በመሳተፍ እንዲመልሱ አበረታቷቸው።

የተማሪዎቹ መልሶች ያለፈውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱና እንደተገነዘቡ ለመለየትና ከአዲሱ ርዕስ ጋር ለማዛመድ ይረዳል። ተማሪዎቹ በሰጡት መልስ ላይ በመመርኮዝ ግብረመልስ መስጠት።

የሰብአዊ መብቶችን መከበር አስፈላጊነትን በማስመልከት አጭር ማብራሪያ በመስጠትና ሲያብራሩ የሚከተሉትን ቁልፍ ነጥቦች ማዕከል ማድረግ፤

ሰብአዊ መብቶች ለሁሉም ሰዎች ከለላ ይሰጣሉ። ሰብአዊ መብት በህብረተሰባችን ውስጥ መልካም እሴት የሆኑትን ሰላም፣ ፍትህ፣ አክብሮት፣ እኩልነት እና መከባበርን ያቀፈ ነው።

ሰብአዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት;

- በመቻቻል አብሮ ለመኖር፣

- በተሳካ ሁኔታ ስራን ለመስራት
- ከጭቆና የጸዳ ማህበረሰብን ለማፍራት፣
- ሃሳብን በነጻነት ለመግለጽ ፣
- የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ፣
- የመንቀሳቀስ ነፃነትን ለማረጋገጥ፣
- ከተጽዕኖ ነጻ ለመሆንና የመሳሰሉት ናቸው።

**ክለሳ፡** የሰብአዊ መብት መከበር አስፈላጊነትን በመግለጽ በዋና ዋና የትምህርቱ ነጥቦች ላይ የዕለቱን ትምህርት መቋጨት።

**ግምገማ፡** የዕለቱ ትምህርት ካለቀ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኘውን ተግባር 2.3 ይጠይቁ።

**የተግባር 2.3 መልስ**

1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት

## *2.3. ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ሰብአዊ መብቶችንና ግዴታዎችን ያነጻጽራሉ።
- ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎችን ይዘረዝራሉ።.
- በመብቶች እና ግዴታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይገልጻሉ።

**አጠቃላይ እይታ፡** ባለፈው ትምህርት ይዘት ውስጥ ተማሪዎች የሰብአዊ መብቶች መከበርን አስፈላጊነት ተምረዋል። በዚህ ትምህርት ደግሞ በመብቶች እና ግዴታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይማራሉ። መብቶች እና ግዴታዎች የማይነጣጠሉ ናቸው። ግዴታህን አለመወጣት በአንተ/አንቺ ላይም ሆነ በሌሎች ላይ ተጽዕኖ አለው።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን ስያጸዱ የሚያሳይ ምስል ወይንም ስዕል መጠቀም።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች፡** የግንዛቤ ጥያቄዎች፤ የቡድን ስራ እና ሪፖርት፡

፡**መግቢያ**፡ ከዕለቱ ርዕስ ጋር ማስተዋወቅ እና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎች በመጠየቅ፤

1. በመብት እና ግዴታ መካከል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

2.ሰዎች ግዴታቸውን ሳይወጡ መብታቸውን ብቻ የሚጠይቁ ከሆነ ምን ሊፈጠር ይችላል? ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ከላይ ባሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ ፡፡

- ውይይታቸውንም መከታተል፡፡
- ለተወሰኑ ተማሪዎች ምላሻቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል መስጠት፡፡

የተማሪዎቹን ሀሳብ በማዳመጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ማዕከል በማድረግ ምላሹን መግለጽ፡፡

**መልስ**

መብቶች እና ግዴታዎች የማይነጣጠሉና **የማይለያዩ** ናቸው፡፡ ስለዚህ መብታችንን አውቀን ግዴታችንን መወጣት ይኖርብናል፡፡ ግዴታችንን አለመወጣት መብታችንን እንዳንጠቀም ሊያደርገን ይችላል፡፡

**ገለጻ**

በመጨረሻ በመብት እና ግዴታ መካከል ያለውን ግንኙነት ማብራሪያ በመስጠት መብቶች እና ግዴታዎች የማይነጣጠሉ መሆናቸውን መግለጽ፡፡ አንድ ሰው መብቱን ሲጠቀም የሌሎችን መብቶች የማክበር ግዴታም አለበት፡፡ ማንኛውም ሰው ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ሲጠቀም የሌሎችን ሰዎች መብት ማክበር ግዴታ አለበት፡፡ የሀሳብ ነጻነትን በመጠቀም ሌላውን መሳደብ የለበትም፡፡ ሰውን መሳደብ የሞራል እና የህግ ጥሰት መፈጸም ነው፡፡ መንግሥት እነዚህን መብቶች የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

ከዚህ በታች መብቶች እና ግዴታዎች ተዘርዝሮ ይገኛሉ።

ተማሪዎች በሌሎች ሰዎች ዘንድ እንዲከበሩ ሌሎችን ማክበር አለባቸው። ሌሎች ሰዎችን ካላከበሩ በሌሎች ሰዎች ዘንድ አይከበሩምና።

**ክለሳ፡** በሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች መካከል ስላለው ግንኙነት በአጭሩ አብራራ/ሪ።

**ግምገማ፡** ከዕለቱ ትምህርት ማገባደጃ በኋላ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች ከተግባር 2.4 መብት እና ግዴታ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል? የመሚለውን በመጠየቅ ትምህርቱን መገምገም።

**የተግባር 2.5 መልስ**

**በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ መብቶችንና ግዴታዎችን በመለየት ሙላ/ይ።**

1. በመብቶች ስር፡-

- በሰላም የመኖር መብት።
- ጥያቄ የመጠየቅ መብት
- ምግብ የማግኘት መብት
- የመማር መብት።

2. በግዴታዎች ስር፡-

- እናትና አባትን የማክበር ግዴታ

- አረጋዊያንን የማክበር
- መምህራንን የማክበር
- የትምህርት ቤት ህጎችንና ደንቦችን የማክበር
- አላስፈላጊ ቃላቶችን ከመናገር የመቆጠብ
- ጎረቤትን የማክበር
- ቤተሰብን የማገዝ
- ከጎጂ ልማዳዊ ድርግቶች የመቆጠብ
- አካባቢን የማጽዳት ግዴታ
- የቤት ስራንና የክፍል ፈተናን ራስን ችሎ የመስራት ኔዴታ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 2.4. ሰብአዊ ክብር

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ሰብአዊ ክብርን መግለጽ።
- ሰብአዊነትን ማክበር።
- የሰብአዊ መብት ጥሰትን ማውገዝ።

**አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርት ተማሪዎች በይበልጥ ስለ የሰው ልጆች ክብር ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**፡ የሰው ልጅ ክብርን የሚያሳዩ ምስሎችንና ስዕሎችን መጠቀም።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎችን፤የቡድን ውይይቶችን፤ ጥያቄና መልስ በመጠቀም ።

**መግቢያ፡** ተማሪዎችን ከዕለቱ ርዕሱ ጋር ማስተዋወቅና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

**የእለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎች በመጠየቅ፤

1. ሰብዓዊ ክብር ምንድን ነው?
2. የክፍል ጓደኞችህን/ሽን ታከብራለህ/ሽ?

ተማሪዎች ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ በማድረግ በዚህ ደረጃ ጥያቄው ልከብዳቸው ስለሚችል ለማበረታታት መሞከር።

**ንባብ እና ገለጻ**

ተማሪዎች የግንዛቤ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ፣ የሰብዓዊ ክብር ምንነትን ማስረዳት። ሰብዓዊ ክብርን የሚጋፉ ምሳሌዎችን በመውሰድ ማስረዳት። ሐሳቡ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል።

ሰብአዊንትን ማክበር ማለት ለራስ እና ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠት ማለት ነው። ለራሳችን ክብር እንደሚንፈልግ ሁሉ ሌሎችንም የማክበር ግዴታ አለብን። “ሲታከብር ትከበራለህ” የሚል አባባል አለ። ይህ ማለት ደግሞ ለሌሎች አክብሮት ካለን ሌሎች ያከብሩናል ማለት ነው። ስለዚህ ቤተሰብህን፣ ጓደኞችህንና /ሽንና ጎረቤቶችህን የሚታከብር ከሆነ በእነርሱ ዘንድ ትከብራለህ ማለት ነው። ሰብአዊነትን የሚጋፉ ድርጊቶች ስድብ፣ አድልዎ፣ ሰውን መናቅ፣ የወንጀል ድርግቶችን መፈጸም፣ ጦርነትና የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ናቸው።

**መልስ**

1. ሰብአዊንትን ማክበር ማለት ለራስ እና ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠት ማለት ነው። ለራሳችን ክብር እንደሚንፈልግ ሁሉ ሌሎችንም የማክበር ግዴታ አለብን። “ስታከብር ትከበራለህ” የሚል አባባል አለ።

2. አዎ ነው።

**ክለሳ**፡ ስለ ሰብዓዊ ክብር አጠር ባለ ገለጻ በማጠናቀቅ ቁልፍ ሀሳቦችን እንደ ተማሪዎች እንዴት ለሰብዓዊነት ክብር መስጠት እንዳለባቸው፣ ልዩነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ተረድተው፣ የሰዎችን ሀሳብ መቀበል መቻል፤ ሀሳብ ሲሰጡ

ስሜታዊ አለመሆንና አለመጩህ የመሳሰሉትን ቁልፍ ሀሳቦች መንገርና መግለፅ ።

**ግምገማ፡** በእለቱ የትምህርት ይዘት ማገባደጃ ላይ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተግባር **2.7** ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መገምገም። በተግባሩ ስር ያሉ ጥያቄዎች ቀደም ተብሎ ውይይት ተደርጎበታል።.ትምህርቱን ለማጠናከር ተማሪዎች መልሶቻቸውን በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ መንገር። በመጨረሻም የማስተካከያ መልስ መስጠትና ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተሉትን ሐሳቦች እንደ መልስ መጠቀም ።

## የተግባር 2.6 መልስ

1. ሰብዓዊ ክብር

2. ንቄት፤ ስድብ፤ ማግለል፤ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ እና ባርነት

## 2.5. የሕፃናት መብቶች መከበር

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የሕፃናት መብቶችን መዘርዘር
- መብቶችን  መተግበር።

**አጠቃላይ እይታ፡** በቀደመው ትምህርት ተማሪዎች ስለ ሰብአዊ ክብር ተምረዋል። በዚህ ትምህርት ደግሞ  ስለህጻናት መብቶች  መከበርን ይማራሉ፡

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ተማሪዎች በትምህርት ቤት በደስታ ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል ወይንም ፎቶዎችን መጠቀም።

**የመማር  ማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎችን፤ ገለጻንና ሪፖርትን በመጠቀም።

**መግቢያ፡** ተማሪዎች ከዕለቱ ርዕስ ጋር ማስተዋወቅ እና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤

1. ልጆች ሊኖራቸው የሚችሉትን ልዩ የሕጻናት መብቶች ዘርዝር/ሪ።

2. እንደ ሕጻንነትህ/ሽ ምን ዓይነት መብቶች አሉህ/ሽ?

ተማሪዎች ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ዕድል መስጠት። መልስ መስጠት ካቃታቸው ደግሞ አቅጣጫ ማስያዝ።

**መልስ**

1. ሁሉም ሕጻናት ልጆች "የህጻናት መብቶች" በመባል የሚታወቁ የራሳቸው የሆኑ ሰብዓዊ መብቶች አሏቸው። እነዚህም መብቶች ነፃ የመሠረታዊ ትምህርት ዕድል የማግኘት መብት፡ የመጫወት መብት፤ በባህላዊ እና ጥበባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የመሳተፍ መብቶችን የማግኘትን ያካትታሉ። በተጨማሪም ህጻናት መረጃ የማግኘት መብት፣ ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ እና የመደመጥ መብት አሏቸው።

ህጻናት ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለምሳሌ ያለ እድሜ ጋብቻ፤ ጠለፋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና ከመሳሰሉት የመጠበቅ መብት አሏቸው። ሌሎችንም ምሳሌዎች ከሰጧቸው በኋላ ከዚህ በፊት በእነርሱ ላይ የደረሰውን የሕጻናት መብት ጥሰት ካለ እንዲያስታውሱ አበረታቷቸው።

2. ህጻናቱ ያሏቸውን መብቶች ይዘርዝሩ።ሀሳባቸውንም በመቀበል ግብረመልስ መስጠት።

ከግንዛቤ ጥያቄዎች በኋላ ስለ ህጻናት መብቶች መከበር በማብራራት አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጧቸው።

በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ዕድመው ከ18 አመት በታች የሆነ ሰው እንደ ህጻን ይቆጠራል። የህጻናት መብቶች ዕድሜአቸውን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ህጻናት ያሏቸው መብቶች ናቸው። ሰብአዊ መብቶች ለህጻናት ሰብአዊ ጥበቃ ይሰጣሉ። ስለዚህ ህጻናት መሆናቸውን መንገር አስፈላጊ ነው። የህጻናት መብቶች በሚከተለው መልኩ ተተንትነዋል፡ ህጻናት በፆታ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በእድሜ እና በሃይማኖት መድልዎ

ሳይደረግባቸው እኩል መብት አላቸው። የጤና እንክብካቤ፣ ነፃ መሰረታዊ ትምህርት ዕድል የማግኘት መብት ፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በባህላዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍ መብት፣ መረጃ የማግኘት መብት፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የመደመጥ መብት አላቸው።

**ክለሳ፡** ስለ ህጻናት መብቶች ዋና ዋና ነጥቦችን እንደገና በመከለስ ህጻናት ሰብአዊ መብቶች እንዳላቸውና ይህም ከ 18 አመት ዕድሜ በታች ለሆኑ ሕጻናት ሁሉ የሚሰራና የሚያገለግል መሆኑን ማስረዳት።

**ግምገማ፡** በዕለቱ ትምህርት ይዘት ማጠናቀቂያ ላይ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተግባር 2.7 ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።

**የተግባር 2.7 መልሶች**

1. የህጻናት መብቶች መከበር ጥቅሞች ምንድናቸው?

2. በሚትኖሩበት አካባቢ የህጻናት መብቶችን የማክበር ሀላፊነቶች እንዴት ይተገበራሉ?

ተማሪዎች በቡድን ሆነው ከላይ በተጠቀሱት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ በማድረግ ሲወያዩ ማበረታታትና በመጨረሻም አጭር ማብራሪያ በመስጠት በማብራሪያው ውስጥ የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት ይቻላል።

**መልስ**

1. የህጻናት መብትን ማክበር ህጻናት ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲጫወቱ ምቹ ሁኔታን መፍጠር። የሚጫወቱበት ቦታ ማመቻቸት። በተጨማሪም አካል

ጉዳተኛ ህጻናት ከሌሎች ልጆች ጋር መብቶቻቸውን እኩል እንዲጠቀሙ ማመቻቸት ነው።. የህጻናትን መብት ማክበር ተማሪዎች በትምህርታቸው የላቀ ውጤት እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋ። ከትምህርት ቤት ውጭም ጥሩ የሆነ ህይወት እንዲኖራቸው ያደርጋል። እንዲሁም በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ከቤተሰቦቻቸዉ ጋር በሰላም መኖር እንዲችሉ ይረዳቸዋል።

2. ህጻናት እንዲማሩ፣ እንዲጫወቱ፣ የቤተሰብ እንክብካቤን ማግኘት እንዲችሉ መደገፍ እና የመሳሰሉት ናቸው።

## *2.6. የሴቶች መብት መከበር*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡

- የሴቶችን መብት መዘርዘር።
- የሴቶችን መብት ማክበር።

**አጠቃላይ እይታ**: በባለፈው የትምህርት ይዘት ውስጥ ተማሪዎች ስለ ህጻናት መብቶች ተምረዋል። በዚህ ትምህርት ደግሞ የሴቶችን መብቶች ስለማክበር ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ሴቶች የመማር መብቶቻቸውን ሲጠቀሙና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሲሳተፉ የሚያሳዩ ምስሎችንና ፖስተሮችን መጠቀም።

**የመማር የማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎችን፤ የቡድን ውይይቶችንና ሪፖርት በመጠቀም።

**መግቢያ፡** የዕለቱን ርዕስ ማስተዋወቅና ከባለፈው የትምህርት ይዘት ጋር ማገናኘት።

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤

1.ሴቶች ከወንዶች እኩል ማንኛውንም ሥራ በየትኛውም ቦታ መሥራት ይችላሉ።

የሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ?

2. የሴቶች መብቶች ምሳሌዎችን ዘርዝር?

ተማሪዎች ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ማድረግ በተጨማሪም የሴቶችን መብቶች መሠረታዊ ሀሳብ በማብራራት ለተማሪዎች ማስተካከያ መስጠት ።

**ገለጻ**

ከተማሪዎቹ መልስ በኋላ ስለሴቶች መብቶች በምሳሌ በማስደገፍ ለተማሪዎች ማብራሪያ መስጠት።

በኦሮሞ ባህል ሴቶች ይከበራሉ ማለትም ዋዩ ናቸው። በኦሮሞ ባህል ዋዩ ክብር ያለው ነገር ነው። ሰቶችን ማክበር ከማህበረሰባችን መልካም እሴት ውስጥ አንዱ ነው። ስለዚህ የሴቶችን መብቶች መጣስ ኢሰብአዊነት ነው። በጾታ እኩልነት ማመንና ማክበር አስፈላጊ ነው። ማንኛውም ዜጋ የፆታ መድልዎን መታገልና በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን እኩልነት መቀበልና መደገፍ ይጠበቅበታል።

መልስ።

1.አዎ።ሴቶች ከወንዶች እኩል ዕድል ቢሰጣቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት ይችላሉ።

2.ሴቶች የመማር መብት፣ መሬት የማግኘት መብት፣ መኖሪያ ቤት እና ንብረት የማፍራት መብት ፤ በሰላም የመኖር መብት አሏቸው። የሴቶች መብት መከበር ለቤተሰብ ህይወት፣ ለአገር ኢኮኖሚያዊ እድገትና ለሰላም አስፈላጊና ወሳኝ ነው።

**ክለሳ፡** ስለሴቶች መብቶች መከበር ዋና ዋና ሐሳቦችንና ነጥቦችን በማንሳት ትምህርቱን ማጠቃለል።

ከዕለቱ የትምህርት ማገባደጃ በኋላ፣ ተማሪዎች በተግባር 2.8 ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ መጠየቅ።

**የተግባር 2.8 መልስ**

ተማሪዎች ይህን ተግባር ከመስራታቸው በፊት ማብራሪያውን እንዲያነቡ ማድረግ። በመቀጠል ተማሪዎች ጥያቄውን ይስሩ።በመጨረሻም ግብረ መልስና ማስተካከያ መስጠት።

በማስተካከያው ውስጥ የሚከተሉትን ሀሳቦች መጠቀም ።

1.የመማር መብት፤መሬት የማግኘት መብት፤የመኖሪያ ቤትንና የንብረት ባለቤትነት መብት

2. ሁሉም የማህበረሰብ አባላት።

## *2.7. የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የአካል ጉዳተኞችን መብቶች መዘርዘር።
- የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር።

**አጠቃላይ እይታ፡** ተማሪዎች በባለፈው ትምህርታቸው ስለሴቶች መብቶች ተምረዋል በዚህ ትምህርት ደግሞ ስለ አካል ጉዳተኞች መብቶች ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** አካል ጉዳተኞች መብቶቻቸውን ሲጠቀሙ የሚያሳዩ ፖስተሮችንና ምስሎችን ለምሳሌ, የመማር መብት፤ምቹ በሆኑ ሕንፃዎች ውስጥ ሲገለገሉና በተለያዩ ተግባራት ውስጥ ስሳተፉ።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የቡድን ውይይት፤ ጥያቄዎችና መልሶች፤ ሪፖርቶች።

**መግቢያ፡** ከእለቱ ርዕስ ጋር ማስተዋወቅና ካለፉት ትምህርቶች ጋር ማገናኘት።

የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣

1. አካል ጉዳተኝነት ምንድነው?

2. አካል ጉዳተኝነትን የሚያስከተሉ ሁኔታዎችን ግለጽ።

በቡድን በመክፈል የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲመልሱ በማድረግ የተማሪዎቹን ስራ በመከታተል ሁሉም ቡድኖች ስራቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ።

## ማብራሪያ

ከግንዛቤ ጥያቄዎች በኋላ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች የማክበር ሐሳብን በምሳሌ በማስደገፍ ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች በሃሳቡ ውስጥ ማካተት ይቻላል።

## መልስ

1. አካላዊ ጉዳት የአንድን ሰው እንቅስቃሴ አካላዊ ችሎታ ጥንካሬንና ፍጥንትን የሚጎዳ የረጅም ጊዜ ክስተት ነው.። አካል ጉዳተኞች ሌሎች ሰዎች ያሏቸውን ሰብዓዊ መብቶች ሁሉ አሏቸው። እንዲሁም ሙሉ ክብርና የመማር መብት አሏቸው።

ስለዚህ አካል ጉዳተኞች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከመንግስት፣ ከማህበረሰቡ እና ከሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ የማግኘት መብት ሁሉም ህንጻዎች፣ መሳሪያዎች፣ ምርቶች፣ መገልገያዎች፣ መሠረተ ልማት፣ ቴክኖሎጂዎች እና አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚና ምቹ በሆነ መንገድ መዘርጋት አለባቸው። የገበያ አገልግሎቶችንና የተለያዩ የስራ አካባቢዎች ክፍት፣ አካታች ምቹና ለአካል ጉዳተኞች እድል የሚሰጡ መሆን አለባቸው።

2. አንድ ሰው በተፈጥሮ ወይም ከተወለደ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች በድንገተኛ አደጋ፣ በበሽታ፣ በህክምና ስህተት እና በመሳሰሉት አካል ጉዳተኛ ሊሆን ይችላል።

7. ክለሳ: ስለ አካል ጉዳተኞች መብቶች ዋና ዋና ሐሳቦችንና ነጥቦችን በመከለስ ትምህርቱን መቋጨት።

8. ግምገማ፡- ከትምህርቱ ማገባደጃ በኃላ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት የግንዛቤ ደረጃ ለመገምገም በተግባር 2.9 ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ።

**የተግባር 2.9 መልስ**

1. የአካል ጉዳተኞችን መብት ዘርዝር/ሪ።

መምህር/ት፣ ተማሪዎች የአካል ጉዳተኞችን መብቶች እንዲዘረዝሩ በማድረግ ምላሻቸውን በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ በመጠየቅ ተማሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ምላሽ ሲሰጡም በማበረታታት ተማሪዎቹን መደገፍ ። በመጨረሻም ማስተካከያ ሲሰጡ የሚከተሉትን ዋና ዋና ሐሳቦችና ነጥቦች መጠቀም።

አካል ጉዳተኞች የሚያበረታታቸውን የተለያዩ ድጋፎችን እንደ ህክምና፣ የስነ ልቦና ድጋፍ፣ የማቋቋሚያ፣ ማህበራዊ ነክ፣ የትምህርት እና ሌሎች አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አሏቸው።

**የተግባር 2.10 መልስ**

ታሪክ

መምህር/ት፣ ተማሪዎች የሎኮን ታሪክ ከመጽሐፋቸው እንዲያነቡና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በቡድን ተወያይተው እንድዲመልሱ ማበረታታት።

ተግባር 2.10

1. ከሎኮ ስኬት ምን ተማራችሁ?
2. ለሎኮ ምን አይነት ድጋፍ ይደረግላታል?
3. ሰዎች ሎኮን የበለጠ እንዴት መርዳት ይችላሉ?

ተማሪዎች ስራቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ በታሪኩ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት።

መልስ

1. ሎኮ ስኬታማ ለመሆን የቻለችው የሚያስፈልጓት ድጋፎች በመምህራኖቿና በጓደኞቿ በኩል ስለሚደረጉላት ነው። ስለዚህ ለአካል ጉዳተኞች አስፈላጊው ድጋፍ ከተሰጠ ውጤታማ መሆን ይችላሉ ማለት ነው ።

2. ሎኮ የመስማት ችግር ስላለባት ፊትለፊት እንዲትቀመጥ ያደርጓታል።

3. ልዩነቶችን በማክበርና በመቀበል፣በማክበር፣ ፍቅር እና እንክብካቤን በማሳየትና በመስጠት የትምህርት ቁሳቁሶችን በመደገፍ አድልዎ ሊወገድ ይችላል።

# ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ ሲታጠቃለል ተማሪዎች ከዚህ የትምህርት ክፍል የተማሩትን እንዲያብራሩ እድል መስጠና ምዕራፉን አጠር በማድረግ ሀሳብ መስጠት። በመጨረሻም ተማሪዎቹ ለክለሳ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ማድረግ ።

**የክለሳ ጥያቄዎች መልስ።**

**ክፍል I ፡ የእውነት/ሐሰት ጥያቄ መልሶች።**

1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት

4. እውነት 5. እውነት 6. እውነት

**ክፍል II፡ የምርጫ ጥያቄ መልሶች።**

1. ለ 2. ሀ 3. መ 4. መ 5. መ

## ክፍል III. ባዶ ቦታ ሙላ/ሀ።

1. መብት

2. ግዴታ

## ክፍል IV፡ አጠር ያለ መልስ።

1. ለአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ ክብር በመስጠት፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለምሳሌ የመኖሪያ ቤት፣ የስራ እድል፣ የትምህርት እድል በመስጠት፣ ሰብአዊ መብቶቻቸውንና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን በማክበር መደገፍ ይቻላል። ዘመናዊ መሣሪያዎች፣ ምርቶች፣ መሠረተ ልማቶች፣ ቴክኖሎጂዎችና አዳዲስ አገልግሎቶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹና ተደራሽ መሆን አለባቸው።

2. ተማሪዎች እንደየትምህርት ቤታቸው ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ ምላሾችን መስጠት ይችላሉ።

## ትምህርት 7፡ የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር

የትምህርቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፡- በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- የአካል ጉዳትን ጽንሰ-ሐሳብ ያብራራሉ
- የአካል ጉዳተኞችን መብት ይዘረዝራሉ።

# ምዕራፍ 3፡ ሰላም

(የተመደበው ጊዜ፡19 ሰዓት)

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች**፡-

- የሰላምን ምንነት ማብራራት;
- ለሰላም አስፈላጊነት ትኩረት መስጠት;
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የአፈታት ዘዴዎችን ማድነቅ;
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ችሎታን ማሳየት፣
- የሰላም እጦት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መለየት።

## *3.1 የሰላም ምንነት*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የሰላምን ምንነት መግለጽ

**አጠቃላይ እይታ፡** ባለፈው ምዕራፍ ስለ ሰብአዊ መብቶች ተምረዋል። በዚህ ትምህርት ደግሞ ስለ ሰላም ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** የመማሪያ መጻሕፍት

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የቡድን ስራ፣የጉዳይ ጥናት፣ የቡድን ውይይት እና ሪፖርት።

**መግቢያ፡** የዕለቱን ርዕስ ማስተዋወቅና ካለፈው ትምህርት የዘት ጋር ማገናኘት።

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎቸን መጠየቅ፤

1. ሰላም ምንድን ነው?

**መመሪያ፡** በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ተማሪዎች አስበውበት እንዲመልሱ አበረታቷቸው።

በመጀመሪያ ተማሪዎች በተናጠል ይስሩ ። ከዚያም በቡድን እንዲሰሩና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎች ካቀረቡ በኋላ ስለ ሰላም ተጨማሪ ማብራርያ መስጠት።

ሰላም በግልም ሆነ በቡድን ከግጭት ነፃ ሆኖ በመተሳሰብና በፍቅር መኖር ሲሆን ከፈጣሪ እና ፍጥረት ጋር ሰላም መሆን ነው። ሰላም በፍቅር እና በመተሳሰብ አብሮ መኖር ነው። ማለትም ጥላቻንና ጥቃትን በማስወገድ አብሮ መኖር ማለት ነው።

**ክለሳ**: የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ማብራራትና መመልከት ያስፈልጋል።

**ግምገማ**፡ የዕለቱ የትምህርት ይዘት ከቀረበ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ፤

## የተግባር 3.1 መልሶች

1. ሰላም ለውጤታማ የመማር ማስተማር የሚረዳው እንዴት ነው?

2. ሰላም ከሌለ ምን ሊፈጠር ይችላል?

**መመሪያዎች**: በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ስለ ሰላም ምንነትና ለመማር ማስተማር ስላለው ጥቅም ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከውይይቱ በኋላ የማስተካከያ ሐሳብ ለተማሪዎች መስጠት።

**መልስ**

1. ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታን ለመፍጠር እና የመማርያ ክፍሎችን ምቹ ለማድረግ ሰላም ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ይህም የመማር ማስተማሩ ሂደት ስኬታማ በሆነ መንገድ እንዲሰጥ ያደርጋል።

2. ሰላም ከሌለ መረጋጋት አይኖርም። የመማር ማስተማር ሥራንና አካባቢን በሠላም መምራት አይቻልም።

**ስለ ሶረሳ ታሪክ**

ስዕሎቹን በማሳየት ተማሪዎች የሶረሳን ታሪክ እንዲያነቡና እንዲወያዩበት በማድረግ በዚህ ውስጥ የሶረሳ ልምድ፣ ከክፍል ጓደኞቹ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ በራስ የመተማመን ስሜቱንና ፣ የመድረክ ንግግር ብቃቱን የውይይት ነጥብ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የሶረሳ ንግግር ዋና ነጥብ ስለ ሰላም መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳብ ፣የሰላም አስፈላጊነት፣ ሰላምን በማረጋገጥ ረገድ የግለሰብ ሚናና ግዴታን ስለመወጣት ነው።

ከውይይቱ በኋላ ዋና ዋናሐሳቦችንና ነጥቦቹን በመከለስ ለተማሪዎች የማስተካከያ ሀሳብ መስጠት።

## *3.2. የሰላም አስፈላጊነት*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የሰላምን አስፈላጊነት መዘርዘር።
- የሰላምን አስፈላጊነት ማድነቅ።

**አጠቃላይ እይታ፡** ባለፈው ትምህርት ስለ ሰላም ተምረዋል። በዚህ ትምህርት, ተማሪዎች ስለ ደህንነት አስፈላጊነት ይማራሉ.

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ቻርት

**የመማር የማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎችንና የቡድን ስራ።

**መግቢያ**፡ የዕለቱን ርዕስ ማስተዋወቅና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

6. የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቀቅ፤

1. ቢያንስ ሦስት የሰላም ጥቅሞችን ዘርዝር/ሪ

2. የሰላም እጦት በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በአገር ደረጃ ምን ሊያስከትል እንደሚችል አብራራ/ሪ።

**መመሪያ፡**ጥያቄዎቹን በመጠየቅ ተማሪዎች ስለ መልሶቹ እንድዲያሰላስሉ አበረታቷታቸው። ተማሪዎች ጥያቄዎቹን በተናጥል እና በቡድን ከሰሩ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ።

**መልስ**

1. ሰላም ለግለሰብም ሆነ ለህብረተሰብና ለአገር ዕድገት መሰረት ነው። በህብረተሰብ ውስጥ መረጋጋትና ዘላቂ ዕድገት ለማምጣት ሰላም መሰረት ነው፡ ፡ ይህ ደግሞ የሕግ የበላይነትን የሚያረጋግጥና መቻቻልንና ማህበራዊ ትስስርን የሚያበረታታ ነው።

በቤተሰብ እና በግለሰብ ደረጃ ሰላም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለመጠበቅ ይረዳል። ሰላም ልዩነቶችን በማቀፍ መቻቻልን ያበረታታል። በማህበረሰብ እና በአገር ደረጃም ለውጥን ያፋጥናል።

2. ለሁለተኛው ጥያቄ የተማሪዎቹ መልስ አይ ከሆነ ተማሪዎቹ በተለያዩ ደረጃዎች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ችግሮች ላይ ይወያዩ።

**ክለሳ**፡ በዚህ ደረጃ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ጠቅለል አድርጎ መከለስ።

**ጥያቄ**፡ ከትምህርቱ በኋላ ስለ ሰላም አስፈላጊነት ጥያቄዎችን መጠየቅ። ሰላም በመማሪያ ክፍል እና በትምህርት ቤት ምን ምን ሚና አለው? ሰላም ለማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ሁሉ መሰረት ነው። ስለዚህ ሰላም በተማሪዎች መካከል ሰላማዊ ግንኙነትን ይፈጥራል ያጠናክራል። ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተስማምተው እንዲሰሩ እና ምቹ በሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲማሩ ያግዛቸዋል።

በተጨማሪም ሰላም ማህበረሰቦችን እንዴት እንደሚያስተሳስር መጠየቅ። ሰላም ህብረተሰቡ ከፍራት ነጻ ሆኖ በሰላምና በፍቅር አብሮ እንዲኖር ያስችላል። በማንኛውም ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉ እና እርስ በርስ እንዲተማመኑ ያስችላቸዋል።

## *3.3 ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶች*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶችን ትለያለህ/ሽ።

**አጠቃላይ እይታ፡** ባለፈው ትምህርት ስለ ሰላም አስፈላጊነት አስተምረዋል። በዚህ የትምህርት ይዘት ደግሞ ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶችን ታስተምራለህ/ሽ፡፡

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ቻርት

**የመማር የማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎች፣ የቡድን ስራና ሪፖርት፡
፡

**መግቢያ፡** ከዕለቱ የትምህርት ይዘት ጋር ማስተዋወቅና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤

በትምህርት ቤት እና በህብረተሰቡ ውስጥ ሰላም የሚሰፍንበት መንገድ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

**መመሪያ፡** ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች ተወያይተው ምላሾቻቸውን እንዲሰጡ በማበረታታት ተማሪዎች በተናጥል ከሰሩ በኋላ በቡድን ተወያይተውበት ለክፍሉ እንድያቀርቡ ማድረግ።

ሰላም የሚሰፍንበትን መንገዶች ለተማሪዎች መግለጽና ማብራራት። ሰላምን ለማስፈን በግለሰቦች እና በመንግስት የሚተገበሩ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። ለምሳሌለ ማህበራዊ ፍትህን ማስፈን፣ የሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ መቻቻል፣ ውይይት እና መደጋገፍን ያጠቃልላል። በቤተሰብ ደረጃ እንደ ፍቅር፣ አንድነት፣ ርኅራኄ፣ ፍትህ፣ መከባበርና ታማኝነት ያሉ በጎ ባሕርያትን በማዳበር ሰላምን ማስፈን ይቻላል።

ተግባር 3.2

1. ሰላም የመማር ማስተማር ስራን እንዴት ሊያግዝ ይችላል?

2. ሰላም ማህበረሰብን ለማገናኘት የሚረዳው እንዴት ነው?

**መልስ**

1. ሰላም ካለ ተማሪዎች ተረጋግተው ይማራሉ፣ መምህራን በተረጋጋ ሁኔታ ያስተምራሉ፣ መንግሥት አስፈላጊውን የትምህርት ቁሳቁስ ማቅረብ ይችላል።

2. ሰላም መተሳሰብና ፍቅር እንዲጎለብት ያግዛል።

**ክለሳ፡** የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች መከለስ

**ግምገማ፡** ከገለጻው በኋላ የተግባር 3.3 ጥያቄዎችን ተማሪዎችን በማሰራት የማስተካከያ መልስ መስጠት።

## ተግባር 3.3

1. በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ውስጥ ሰላምን የማስፈን መንገዶችን በቡድን በመወያየት ለክፍል ጓደኞቻቸው አቅርቡ።

2. ሰላምን በማስፈን ረገድ የወላጆች ሚና ምንድን ነው?

**መመሪያ**: በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ሰላምን የማስፈን ዘዴዎችን መጠየቅ። ተማሪዎችም አንዳንድ ዘዴዎችን በመዘርዘር እንዲወያዩበቸው ማድረግ ።

## መልስ

1. ለምሳሌ በቤተሰብ ደረጃ ፍቅርን፣ አንድነትን፣ ርህራሄን፣ ፍትህን፣ መከባበርንና ታማኝነትን ማሳደግ።

ተማሪዎች የተቀሩትን በራሳቸው እንዲዘረዝሩና እንዲወያዩበት ማበረታታት።

3. ተማሪዎች ሰላምን ለማስፈን የወላጆቻቸውን ሚና ይወያዩበት። በመጨረሻም የማስተካከያ ሃሳብ በመስጠት የዕለቱን የትምህርት ይዘት ማጠናቀቅ ይቻላል።

## *3.4 ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፈታት*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

የግጭት አፈታት ምንነትን መግለጽ;

ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ዘዴዎችን መዘርዘር።

**አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ስለመፍታት ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ምስሎች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎች፣ የቡድን ውይይትና ውስን ጥናት።

**መግቢያ፡** ከዕለቱ ትምህርት ጋር ማስተዋወቅና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤

- የግጭት አፈታት ሂደት ማለት ምን ማለት ነው?

መመርያ፡ ይህንን ጥያቄ በመጠየቅ ተማሪዎች አሰላስለው እንዲመልሱ ማበረታታት ።

እያንዳንዱ ተማሪ በግል ከሰራ በኋላ በቡድን ሰርተው ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ።

ግጭትን በሰላማዊ መንገድ እንዴት መፍታት እንደሚቻል ለተማሪዎች ማብራራት።

**መልስ**

ሰላማዊ የግጭት አፈታት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል ለሚፈጠረው ግጭት ሰላማዊ መፍትሄ ማምጣት ነው። ግጭቱም ከማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም ስለ ቢቂላ እና ጉደታ ትረካ አስመልክቶ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ይወያዩ።

**የተግባር 3.4. መልስ**

በትምህርቱ መጨረሻ ላይ  የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ።

1. ቢቂላ እና ጉደታ በመጨረሻ ምን ወሰኑ? ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ዓሣውን አብስለው  ለመብላት ወሰኑ።

2. በቢቂላ እና ጉደታ መካከል የተፈጠረው ግጭት መንስኤው ምንድን ነው? ዓሣ

3. በዓሣው ላይ የተነሳው አለመግባባት እንዴት ተፈታ? ሁለቱም ዓሣውን በጋራ ለመጠቀም በመስማማታቸው።

4. የዚህ ታሪክ እሴቶች ምንድን ናቸው?

- መቻቻል፣በጋራ መጠቀም፣እርቅ፣ይቅር ባይነት፣ለሽማግሌዎች መታዘዝ።

**ክለሳ፡** ስዕሉን በማሳየት ተማሪዎች ታሪኩን አንብበው እንዲወያዩበት በማድረግ። የግጭቱን መንስኤ፣ ያስከተለውንና እንዴት መፍታት እንደሚቻል ተማሪዎቹ ይወያዩበት። በተመሳሳይ መልኩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ግጭቶችን በባህላዊ መንገድ እንዴት በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንደሚቻል፣ የሚመራባቸው ደንቦች፣ የሚመለከታቸው አካላት እና የመፍትሄ ሃሳቦች ናቸው።

***ግምገማ***፡ ከገለጻው በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ።

የተግባር 3.5 መልስ

1. በማህበረሰቡ ውስጥ ግጭቶችን ለመፍታት የሀገር ሽማግሌዎች ትልቅ ሚና አላቸው ።

2. አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፈታት ሂደት ውስጥ ሽማግሌዎች በተጋጩ ወገኖች ይመረጣሉ።

ተማሪዎች ከጥያቄ 3-5 ድረስ ያሉትን ከተወያዩበት በኋላ የማጠቃለያ ሀሳብ መስጠት።

3. በአካባቢያችሁ ሽማግሌ ሆነው በማገልገል የሚታወቁትን የአምስት ሰዎችን ስም ዘርዝሩ።

4. በአካባቢያችሁ ግጭቶች እንዴት ይፈታሉ?

5. በትምህርት ቤት እና በክፍል ውስጥ ሰላምን ለመጠበቅ ማድረግ ያለባችሁን ነገሮች ጻፉ።ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ የግጭቱን መንስኤ መለየት፣ የመፍትሄ

አማራጮችን መዘርዘር እና ውሳኔ መስጠትን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች መደረግ አለባቸው።

## *3.5. የሰላም እጦት የሚያስከትለው ጉዳት*

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የሰላም እጦት የሚያስከትለውን ጉዳት መዘርዘር።

**አጠቃላይ እይታ፡** ባለፈው የትምህርት ይዘት ውስጥ ተማሪዎች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ዘዴዎችን ተምረዋል። በዚህ የትምህርት ይዘት ደግሞ የሰላም እጦት ስለሚያስከትለው ጉዳት ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ምስሎች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የግንዛቤ ጥያቄዎች፣ የቡድን ውይይት እና ውስን ጥናት።

**መግቢያ፡** ከዕለቱ ትምህርት ጋር ማስተዋወቅ እና ካለፈው ትምህርት ጋር ማገናኘት።

የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡ የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤

- ግጭት ምን ዓይነት ጉዳት ያስከትላል?

**መመሪያ፡** ከላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ ተማሪዎችን በመጠየቅ አስበውበት እንዲመልሱ ማበረታታት።

እያንዳንዱ ተማሪ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተናጠል በመስራት ምላሹን ለክፍል ጓደኞቻቸው ማቅረብ አለባቸው ።

የሰላም እጦት የሚያስከትለውን ጉዳት ለተማሪዎች ማብራራት ። የሰላም እጦት የሀገርን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ይጎዳል። አለማግባባት ወደ ተግባር ሲቀየር ብዙ ችግሮችን ያስከትላል። ለምሳሌ የአካል ጉዳትና ሞት፣የሰዎች

መፈናቀል፣ሕጻናት በጦርነት የመሳተፍና የበሽታ መስፋፋት ልጠቀሱ ይችላሉ። በተጨማርም የግብርና ምርት፣ ኢንዱስትሪ፣ ንግድ እና መሠረተ ልማቶችም ይጎዳሉ። በተጨማሪም ማህበራዊ ችግሮች፣ የአካባቢ ጎዳት፣ ወታደራዊ ወጪ መጨመርና በትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች ላይ የሚደርሰው ጥቃት የጸጥታ ማጣት ውጤቶች ናቸው።

**ክለሳ፡** የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ጠቅለል አድርጎ ማቅረብ።

***ግምገማ፡*** በመጨረሻም ግጭት የሚያደርሰውን ጉዳት ተማሪዎችን መጠየቅ።

የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

ክፍል I. የእውነት / ውሸት ጥያቄ መልሶች

1. ውሸት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት

ክፍል II. ምርጫ

1. መ 2. መ 3. መ 4. ሐ

ለጽሑፍ ጥያቄዎች ተማሪዎች ከተማሩት ትምህርት የተረዱትን እንዲጽፉ መጠየቅ።

# ምዕራፍ 4: በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚያስፈልግ ሥነ-ምግባር (የተሰጠው ክፍለ-ጊዜ:- 21 ሰዓት)

የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ:-

- የሥነ-ምግባርን ፍች መግለጽ፤
- በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሥነ-ምግባርን አስፈላጊነት መግለጽ፤
- የእረፍት ጊዜን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ መግለጽ፤
- በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት መለየት፤
- ለመንገድ ትራፊክ ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መለየት፤
- በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ አስፈላጊ ለሆኑ የሥነ-ምግባር መርሆዎች እውቅና መስጠት፤

## 4.1. የሥነ-ምግባር ምንነት

1. ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች:-
   - የሥነ-ምግባርን ምንነት ይገልጻሉ፤
   - በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያስፈልጉ መልካም ምግባሮችን ይዘረዝራሉ።

2.አጠቃላይ ሁኔታ:- በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የሥነ-ምግባርን ፍች በጥልቀት ይማራሉ።

3.የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች:- የሥነ-ምግባር መሰረታዊ ደንቦችን የሚያመላክቱ ዲያግራሞችን በመጠቀም ማስተማር

4.የመማር ማስተማር ዘዴ:-የግንዛቤ ጥያቄ፣ የመወያያ ጥያቄ፣ጥያቄና መልስ

5.መግቢያ:-ያለፈውን ትምህርት በማስታወስ ከዕለቱ ትምህርት ጋር ማያያዝ፣ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ መንገርና ሊጎናጸፉት የሚገባውን ዝቅተኛውን የመማር ብቃት ግልጽ ማድረግ

6.አቀራረብ:- የግንዛቤ ጥያቄ፣ "መልካም የሚባሉት ተግባራትና ጸያፍ የሚባሉት ተግባራት የትኞቹ ናቸው?" የሚል ጥያቄ ጠይቃቸው። ይህ ጥያቄ  በቃል መጠየቅ አለበት።ተማሪዎችም በቃላቸው በሕብረተሰቡ ዘንድ መልካምና ጸያፍ የሚባሉ ተግባራትን እንዲዘረዝሩ አበረታታ/ቻቸው።

ጽብረቃ፡- በተማሪዎቹ ሃሳብ ላይ በመንተራስ መምህሩ ግብረ-መልስ መስጠት ይጠበቅበታል።

## ማንበር/ማብራራት

መምህር፡- ሥነ-ምግባርን በሚመለከት አጠር ያለ ማብራሪያ ስጥ/ጪ።

ይህም:-

- የሥነ-ምግባር ፍችና
- የሥነ-ምግባር ባህርያትን ከምሳሌዎቻቸው ጋር አጠር በማድረግ ማብራሪያ ስጥ/ጪ።

ሥነ-ምግባር መልካምና ጸያፍ ተግባራት የሚለይበት መስፈርት ነው። ሥነ-ምግባር መልካም ተግባራትን ወይም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ተግባራት የሚንጸባረቁበት ነው። ጸያፍ ተግባራት ደግሞ በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸውና የሚጠሉ ተግባራት ናቸው። በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ተግባር መፈጸም መልካም ተግባር ሲሆን ሥነ-ምግባር አለመላበስ ደግሞ ጸያፍና በማሕበረሰቡ ተቀባይነትን ማጣት ነው። የመልካም

ተግባራት ምሳሌ የሆኑት ታማኝነት፣ አክብሮት፣ ሃላፊነት መውሰድ፣ እውነተኛነትና እንክብካቤ ማድረግ ናቸው። ጸያፍ ተግባራት ደግሞ መዋሸት፣ መስረቅ፣ ማጭበርበር፣ ከሰው መጣላት፣ ሰው መጥላት ወዘተ. ናቸው።

7. ማጠናከሪያ፡- የሥነ-ምግባርን ፍቺና የመልክም ባህርያትን ተግባራት የሚመለከቱ ዋና ዋና ሃሳቦችን መግለጽ

8. ምዘና

ተማሪዎች እንዲያገኙት የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት መጎናጸፋቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎች በተማሪዎች መጽሓፍ ላይ የቀረቡትን በተግባር 4.1 እና 4.2 ሥር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ጠይቃቸው/ቂያቸው።

**የተግባር 4.1 መልስ**

መምህር ፡- እስኪ በቅድሚያ ተማሪዎች እነኚህን ተግባራት እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ አድርግ/ጊ።መልስ ከሰጡ በኋላ መልሶቻቸውን ከዚህ በቀረበው መሰረት ማስተካከያ በመስጠት አበታታቸው/ቻቸው።

ሥነ-ምግባር መልካምና ጸያፍ ተግባራትን እንዲሁም ትክክል እና ስህተት የሆኑ ተግባራትን የሚመረምር ነው። ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ በማድረግ ሒደት ውስጥ ወላጆች፣ አሳዳጊዎችና ትምህርት ቤቶች ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው። በተለይም ትምህርት ቤቶች መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸውንና የህብረተሰቡን እሴት የሚያከብሩ ዜጎችን ለማፍራት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት መስራት ይጠበቅባቸዋል።እነኚህ እሴቶችም፡- ወላጆችንና ታላላቆችን ማክበር፣ የትምህርት ቤትን ደንቦችና የክፍል ውስጥ ሥርዓቶችን ማክበር፣ የትምህርት ቤቶችን ንብረት ከጥፋት መጠበቅና መንከባከብ፣ ትምህርት ቤቱን ለማስዋብ በሚሰራ ስራ ላይ መሳተፍ የመሳሰሉትን ባህርያት

እያጎለበቱ እንዲሄዱ መርዳት ይገባል።በተጨማሪም ጸያፍ ተግባራትን ማለትም ከመዋሸት፣ ማጭበርበር፣ ኩረጃ፣ አለመታዘዝ፣ ሰዓት አለማክበር፣ የቤት ስራ አለመስራት፣ መጽሐፍና ደብተር ሳይይዙ ወደ ክፍል ከመምጣት ወዘተ. እንዲጠነቀቁ ማድረግ ያስፈልጋል። እስኪ መምህር የክፍሉን ተማሪዎች ልጆች መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሱ ማድረግ ላይ ወላጆች ያላቸውን ድርሻ ቤተሰቦቻቸውን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ አበረታታቸው/ቻቸው።

## የተግባር 4.2 መልስ

መምህር፡- እስኪ ተማሪዎች በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ “መልካም ተግባራት” ወይም “ጸያፍ ተግባራት” በማለት ”√” ምልክት በማድረግ እንዲለዩ ድጋፍ አድርግ/ጊላቸው። መልሱን ከታች በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ ማቅረባቸውን አረጋግጥ/ጪ።

| **ተ.ቁ** | **ተግባር/ባህርይ** | **መልካም ተግባር** | **ጸያፍ ተግባር** |
|---|---|---|---|
| 1 | የትምህር ቤቱንና የመማሪያ ክፍልን ደንብ ማክበር | √ | |
| 2 | በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኙ አይነ-ስውር ተማሪዎችን መርዳት | √ | |
| 3 | ከሰዎች ጋር አለመግባባት | | √ |
| 4 | ወላጆችንና አዛውንቶችን ማክበር | √ | |
| 5 | በአካባቢ እንክብካቤ ሥራ ላይ መሳተፍ | √ | |
| 6 | ምስጢር መጠበቅ | √ | |
| 7 | እውነት መናገር | √ | |
| 8 | ሐሰት መናገር | | √ |
| 9 | መስረቅ | | √ |

## 4.2. በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሥነ-ምግባር አስፈላጊነት

ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝቅተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- ሥነ-ምግባር በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ይለያሉ፡፡
- መልካም ተግባራት የሚታዩባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፡፡

2. አጠቃላይ ሁኔታ፡-ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ውስጥ ሥነ-ምግባር በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ይማራሉ፡፡
3. የትምህር መርጃ መሳሪያዎች፡- ሕጻናት በማህበረሰብ ድጋፍ ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ የሚያመለክት ሥዕል

4.የመማር ማስተማር ዘዴ፡- የቡድን ውይይት፣ ሚና ጨዋታና የተግባራት ጽብረቃ

5. መግቢያ:-የትምህርቱን ርዕስ ማስተዋወቅና ካለፈው ትምህርት ጋር ማያያዝ

6. አቀራረብ:-

የግንዛቤ ጥያቄ

1. በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ሥነ-ምግባር አስፈላጊ ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ? በማለት ጠይቅ/ቂ፡፡

መምህር፣ ተማሪዎች ይህንን ጥያቄ እንዲመልሱ አበረታታቸው/ቻቸው፡፡ በተጨማሪም በንቃት እንዲሳተፉ ደግፏቸው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ ትምህርቱን ምንያህል ለመለየትና አዲሱን ትምህርት ለመጀመር አቅጣጫ ያሳየሃል/ሻል፡፡

አጭር ማብራሪያ ስጥ/ጪ፡፡

መምህር፡- ሥነ-ምግባር በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት በሚመለከት አጠር ያለ ማብራሪያ ለተማሪዎች ስጥ/ጪ። የሚሰጠው ፣ ማብራሪያም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነጥቦች ሊያካትት ይችላል።

- ☞ ሥነ-ምግባር በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ በሁሉም አቅጣጫ አስፈላጊ ነው። ጥሩ ዜጋ ለመሆን መልካም ሥነ-ምግባር መላበስ ወሳኝ ነው። በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት፣ መወደድና መከበር የሥነ-ምግባር መላበስ መገለጫዎች ናቸው። በተጨማሪም ሰዎችን በእኩልነት ለማየት፣ በስራ ስኬታማ ለመሆን፣ ጭንቀትን ለማስወገድና ማህበራዊ ኑሮን ለማሻሻል ወዘተ፣ ያግዛል።

7. ማጠናከር:- ሥነ-ምግባርንና ባሕርያቱን በሚመለከት ዋና ዋና የሆኑ ነጥቦችን በመከለስ ለተማሪዎች ግለጽ/ጪ።

8. ምዘና:- ተማሪዎች እንዲያገኙት የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት መጎናጸፋቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎች በተማሪዎች መጽሓፍ ላይ የቀረቡትን በተግባር 4.3 የቀረቡትን ጥያቄዎችእንዲመልሱ ጠይቃቸው/ቂያቸው።

**የ 4.3 ተግባራት መልስ (በግል የሚሰራ የቤት ስራ)**

መምህር፡-ተማሪዎች በደብተራቸው ላይ የተሰጣቸውን መልመጃ እራሳቸውን ችለው መስራታቸውን በመመልከት አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎችን አድርግ/ጊ። በተመሳሳይ ሁኔታ በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ሥነ-ምግባር ያለውን አስፈላጊነት በሚመለከት ማብራሪያ አክልበት/ዪበት።

| ተ.ቁ | ተግባራት/ባህርያት | መልካም ተግባር | ጸያፍ ተግባር |
|---|---|---|---|
| 1 | ሐዊ የእርስዋን አርሳስ ከሚልኬሶ ጋር በጋራ ይጠቀ፣ ሉ። | √ | |
| 2 | አብዲ ለወላጆቹና ለጎረቤቶቹ አክብሮት አለው። | √ | |
| 3 | ቦሩ ሌንሳ ጠፍቶባት የነበረውን መጽሐፍ አግኝቶ ሰጣት። | √ | |
| 4 | ጫለቱ ያለተራዋ ከጓደኞችዋ ጋር መጫወት ትፈልጋለች። | | √ |
| 5 | ደራራ በብስክሌት ላይ ሲወድቅ ኦላና ድጋ አደረገለት። | √ | |
| 6 | ኢፍቱ ኦብሴን ሥራ ረዳቻት። | √ | |

## 4.3. የእረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- የእረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ምንነት መግለጽ፤
- የእረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም አስፈላጊነት ይለያሉ።

2. አጠቃላይ ሁኔታ :- በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የእረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ይማራሉ።

3. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች :- የለሊት ወፍ ሥዕል ማሳየት

4.የመማር ማስተማር ዘዴ፡-የቡድን ውይይትና ሚና ጨዋታ

5. መግቢያ:- ባለፈው ትምህርት የተማሩትን ዋና ዋና ነጥቦች አስታውስ/ሺ። የአዲሱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ንገራቸው/ሪያቸው። ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎናጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው።

6. አቀራረብ:- አጭር ማብራሪያ ከመሰጠቱ በፊት የተማሪዎችን ግንዛቤ በመጠየቅ ጀምር/ሪ።ለምሳሌ፡- የእረፍት ጊዜ ምንነት፣ የእረፍት ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም አገልግሎት፣ ስለ እረፍት ጊዜ የሚያውቁትን እንዲናገሩ አበረታታ/ቺ። . እነኚህን ጥያቄዎች ተማሪዎች በራሳቸው እንዲመልሱ እድል ስጣ/ጫቸው። በተማሪዎቹ የተሰጠውን መልስ ካዳመጥክ/ሽ በኋላ የእረፍት ጊዜ ምንነትና አስፈላጊነት ላይ እንዲሁም የእረፍት ጊዜያቸውን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አጭር ማብራሪያ ስጥ/።

**አጭር ማብራሪያ**

የእረፍት ጊዜ ከመደበኛ የስራ ሰዓት ለተወሰነ ጊዜ ነጻ መሆን ነው። የእረፍት ጊዜ ለሰው ልጅ ኑሮ አስፈላጊ ነው።ይህም የሰውን አእምሮ ለማደስና ለሰው ኑሮ ጤና ለመስጠት ያገለግላል። የእረፍት ጊዜን ከመደበኛ የስራ ሰዓት ለየት በማድረግ በመዝናናት፣ መጫወት፣ ቅርሶችን መጎብኘት፣ ተክሎችን መንከባከብ፣ ከቤተሰብና ጓደኛ ጋር በጥሩ ሁኔታ በማሳለፍ ሊገለጽ ይችላል። በተጨማሪም መጻሕፍትን በማንበብ፣ በአካባቢያችን የሚገኝን የሚዚቃ መሳሪያ በመጫወት፣ በስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍና መመልከትን ያካትታል።

7. ማጠናከሪያ:- የእረፍት ጊዜን በአግባቡ መጠቀምን በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አጠር በማድረግ ግለጽ/ጪላቸው።

8. ምዘና:-ተማሪዎች እንዲያገኙት የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት መጎናጸፋቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎች በተማሪዎች መጽሓፍ ላይ የቀረቡትን በተግባር 4.4 የቀረቡትን ጥያቄዎችእንዲመልሱ ጠይቃቸው/ቂያቸው።

**የተግባር 4.4 መልስ**

መምህር:-ተማሪዎች “የለሊት ወፍ ትረካ” የሚለውን ጽሑፍ እንዲያነቡ ንገራ/ሪያቸው። በምንባቡ ላይ በመመስረት የቤት ስራውን እራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ አቅጣጫ ስጣ/ጫቸው።የቤት ስራቸውን በማረምና በማስተካከል አበረታታ/ቻቸው ።በመጨረሻም ተማሪዎች የእረፍት ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀም በኑሮአቸው ውስጥ አጥጋቢ ውጤት ማስገኘት እንዲችሉ ጠንክረህ/ሽ አሳስባቸው/ቢያቸው።

- በዚህ ትረካ ውስጥ የለሊት ወፍ የእረፍት ጊዜዋን በአግባቡ መጠቀም አልቻለችም። በጣም ሰነፍ ስለሆነች በዝናብና በጭቃ ውስጥ ሄጄ አልሰራም በማለት ጊዜዋን በስንፍና ስታሳልፍ ነበር። ሌሎች ወፎች ግን የእረፍት ጊዜያቸውን በአግባቡ በመጠቀማቸውና የነበረባቸውን ብድር በወቅቱ ስለከፈሉ በደስታ ይኖራሉ። የለሊት ወፎች ግን ብድራቸውን መክፈል ባለመቻላቸው ዘመናቸውን በሙሉ ለሊት ለሊት በመሄድና ቀን ቀን ሰዎችን በመደበቅ ይኖራሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ሕጻናት የእረፍት ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙና ስንፍና እንዳይኖርባቸው ትረካውን በሚገባ ማስገንዘብ ወሳኝ ነው።

## በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት

መምህር፡-ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ በጋራ እንዲሰሩ አድርግ/ጊ። በመጨረሻም ተማሪዎቹ የሰሩትን በማረም መግለጫ በሚያስፈልገው በታ ምሳሌዎችን በመስጠት አስረዳ/ጃቸው።.

1) ስንፍና ምን ሊያስከትል ይችላል?
2) “ ምከረው ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው ” የሚለው ተረት ምን ያስገነዝበናል?
3) በእረፍት ጊዜና በሰራ ጊዚ መሃከል ያለውን ልዩነት ተወያዩበት።.

## 4.4. በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራትን መለየት፤
- በማህበረሰቡ ተቀባይነት የሌላቸውን ተግባራት በመፈጸም ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ይገልጻጻሉ።

2. አጠቃላይ ሁኔታ፡- በዚህ ትምህርት ውስጥ የማሕበራዊ ኑሮን ምንነት፣ እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ተቀባይነት ስላላቸውና ስለሌላቸው ተግባራት ለይተው ይማራሉ።

3. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡- ተጨባጭ ቁሳቁሶችን ወይም ሥዕሎችን በማሳየት መጠሪያ ስማቸውን መንገር፤

4. የመማር ማስተማር ዘዴ፡- የቡድን ውይይት፣የግል ስራ፣ሚና ጨዋታና ጉዳዮችን መመርመር፤

5.መግቢያ፡-የእለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይዝ/ዢ። ያለፈውን ትምህርት ዋና ዋና ይዘቶች አስታውሳ/ሻቸው። ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎናጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው።

6. አቀራረብ፡-

መምህር፡- ተማሪዎች ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ቅድሚያ ስጣ/ጪቸው። ማሕበራዊ ኑሮ ማለት ምን ማለት ነው? በማሕበራዊ ኑሮ

ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት መለየት ለምን አስፈለገ? በትምህርት ቤት ውስጥና በአካባቢህ/ሽ በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት ለይተህ/ሽ መግለጽ ትችላለህ/ሽ? የተሰኙትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታቸው/ቻቸው።

## አጭር ማብራሪያ መስጠት

መምህር፡-በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ተቀባይነት ባላቸውና በሌላቸው ተግባራት ላይ አጭር ማብራሪያ ስጥ/ጪ።

- ☞ ማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ማለት ማህበረሰቡ በኑሮው ውስጥ የለመዳቸውና የሚተገብራቸው ተግባራትን የሚመለከት ነው። እነኚህ የተለመዱ ተግባራት በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያገኙ ሲሆኑ፣ ጸያፍ ተግባራት ደግሞ ማህበረሰቡ የሚያወግዛቸው ተግባራት ናቸው። በዚህ መሰረት በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች መከናወን ያለባቸውና የሌለባቸው ተግባራት ለምሳሌ ሕጻናት በመኖሪያ ቤት ውስጥ እንዲንጸባረቅባቸው የሚጠበቁ ባህርያት ጥቂቶቹ፡- አባትና እናትን ማክበር፣ ታላቅን ማክበር፣ ተራ ጠብቆ መናገር፣ ወላጆችን በስራ መርዳት እና ወዘተ. በመኖሪያ ቤት አካባቢ የአካባቢን ንጽሕና መጠበቅ፣ እጽዋትን መንከባከብ፣ እንዲሁም በመንገድ ላይ ትላልቅ ሰዎችን ማክበር፣ መርዳት፣ የአካል ጉዳተኞችን መደገፍና በትምህርት ቤት አካባቢም የትምህርት ቤት ደንቦችንና የክፍል ውስጥ ሥርዓቶችን ማክበር ይጠቀሳሉ። ስለዚህ በምህበራዊ ኑሮ ውስጥ ሊተገበሩ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ከተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የተጠቀሱትን

የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም ተማሪዎችህ/ሽን ማስገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

7. ማጠናከሪያ፡- በማሕበራዊ ኑሮ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ተግባራትን በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን በአጭሩ ግለጽ/ጪ፡፡

8. ምዘና፡- ተማሪዎች እንዲያገኙት የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት መጎናጸፋቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎች በተማሪዎች መጽሓፍ ላይ የቀረቡትን በተግባር 4.5 እና 4.6 የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ጠይቃቸው/ቂያቸው፡

**የ 4.5 ተግባር መልሶች**

መምህር፡- ተማሪዎች በተግባር 4.5 ስር በመጽሐፉ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሠጡ አድርግ/ጊ፡፡የሚሰጡትን መልስ በመከታተል ግብረ-መልስ ስጣቸው/ስጫቸው፡፡

**ተግባር 4.5**

1.በአካባቢያችሁ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸውን ተግባራት ወላጆቻችሁን በመጠየቅ አምስት ነጥቦችን በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

2. ከታች በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን

| **ተ.ቁ** | **ተግባራት/ባህርያት** | **መልካም ተግባር** | **ጸያፍ ተግባር** |
|---|---|---|---|
| 1 | ወላጆችን፣ መምህራንንና አዛውንቶችን ማክበር | ✓ | |
| 2 | ማርፈድ | | ✓ |
| 3 | በፕሮግራም አለማጥናት | | ✓ |
| 4 | የተቸገረን ሰው ባለን አቅም መርዳት | ✓ | |
| 5 | በፈተና ወቅት መኮራረጅ | | ✓ |
| 6 | ለታላላቆቻችን መታዘዝ | ✓ | |
| 7 | ጊዜን በአግባቡ መጠቀም | ✓ | |
| 8 | ሰዎችን ማታለል/መዋሸት | | ✓ |
| 9 | ከጓደኛ ጋር መጣላት | | ✓ |
| 10 | የትምህርት ቤትን ንብረት ማጥፋት | | ✓ |

## የተግባር 4.6 መልስ

መምህር፡-የተግባር 4.6 መልስ ሰሬቲና ኦብሳን በሚመለከት በተማሪዎች መጽሐፍ የቀረበውን ታሪክ በማንበብ ተማሪዎች ትክክለኛውን መልስ እንዲሰጡ በመከታተል አበረታታቸው/ቻቸው።

# 4.5. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ምንነት ትናገራለህ/ሽ።
- ልንከተላቸው የሚገቡ የመንገድ ትራፊክ ደህንነቶችን ትለያለህ/ሽ ።

2. አጠቃላይ ሁኔታ:- በዚህ ትምህርት ውስጥ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን እንዲሁም ልንከተላቸው የሚገቡ የትራፊክ ደንቦችን ይማራሉ።

3. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡- የትራፊክ ደንቦችንና የፖሊስን እንቅስቃሴ እንዲሁም የዜብራን ምልክት የሚገልጸውን ሥዕል በማሳየት መንገር

4. የመማር ማስተማር ዘዴ፡- የግንዛቤ ጥያቄ፣ የቡድን ውይይት፣ የግል ሥራ፣ ሚና ጨዋታ

5.መግቢያ ፡- የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይዝ/ዢ።ያለፈውን ትምህርት በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አስታውስ/ሺ።.ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎናጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው።

6. አቀራረብ ፡-

☞ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት አለማክበር የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን እንደሆኑ ተማሪዎችን በመጠየቅ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታ/ቺ።

## አጭር ማብራሪያ መስጠት

መምህር፡-የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን በሚመለከት ለተማሪዎች ሊረዱት በሚያስችላቸው መንገድ ግልጽና አጭር ማብራሪያ ስጥ/ጪ።

✍ የመኪና መንገድ ማለት ተሽከርካሪዎች በብዛት የሚንቀሳቀሱበት መንገድ ነው። የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ደግሞ በሕይወትና በንብረት ላይ ሊደርስ ከሚችል አደጋ ለመዳን የሚደረግ ጥንቃቄ ነው። ያለ ጥንቃቄ የመኪና መንገድ ላይ መዳዝም ሆነ በሩጫ ማቋረጥ ክልክል ነው። የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዓላማም በመኪና አደጋ ሊመጣ የሚችልን እንደ ሞት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት የመሳሰሉ ጉዳቶችን መቀነስ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡም ሆነ ወንዝ ሲሻገሩ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም ተማሪዎችምን ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው።

## 7. ማጠናከሪያ፡-የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን በአጭሩ ግለጽ/ጪ።

8. ምዘና፡-ከዚህ ትምህርት ማብቂያ በኋላ ተማሪዎች የሚፈለገውን ችሎታ ማግኘታቸውንና ከሚፈለገው ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ በተግባር 4.7 ስር የቀረቡ ጥያቄዎችን ተማሪዎች እንዲመልሱ ጠይቃቸው።

**የተግባር 4.7 መልስ**

መምህር፡- ተማሪዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የመንገድ ትራፊክ ደህንነቶችን ማለትም ከመኪና መንገድ ላይ መጫወት ወይም መሯሯጥን መተው፣ መንገድ ከማቋረጥ በፊት ግራና ቀኝ ማየት፣ መንገድ ስናቋርጥ በዜብራ ምልክት ላይ ብቻ መጠቀም፣ ከተፈቀደው ቦታ በስተቀር በሌላ ቦታ መንገድ ለማቋረጥ አለመሞከር፣ መንገድ ስናቋርጥ ሰዎችን ወይም ስልክ አለማናገር፣ በአደባባይ ላይ ፈጽሞ ለማቋረጥ አለመሞከር፣ ብስክሌት በምንነዳበት ጊዜ የብስክሌቱን ደህንነት ማረጋገጥ፣ ከመኪና ስንወርድ መኪናው በአግባቡ እስኪያቆም ድረስ መጠበቅ፣ እንዲሁም ቀስ ብሎ መውረድና የመሳሰሉትን ጥንቃቄች ማድረግ ከተማሪዎች እንደሚጠበቅ ማሳወቅ ይገባል፡፡

## 4.6. በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚያስፈልጉ የሥነ-ምግባር መርሆዎች

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን አስፈላጊነት ይለያሉ፡፡

2. አጠቃላይ ሁኔታ፡-በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚያስፈልጉ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ይማራሉ፡፡

3.የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-የማሕበራዊ አገልግሎቶችን የሚያሳዩ ሥዕሎችን፣ ቻርቶችን ወዘተ በማሳየት መገልገል

4.የመማር ማስተማር ዘዴ፡- የግንዛቤ ጥያቄ፣ የቡድን ውይይት፣ የግል ስራ፣ ሚና ጨዋታ

5. መግቢያ፡-የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይዝ/ዢ፡፡ያለሰውን ትምህርት በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አስታውስ/ሺ፡፡.ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎነጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው፡፡

6. አቀራረብ ፡- መምህር፡- በማሕበራዊ አገልግሎት ውሥጥ ሥራ ላይ የሚውሉ መርሆዎች የትኞቹ ናቸው? የሥነ-ምግባር መርሆዎች በማህበራዊ አገልግሎት ውስጥ ምን ጠቀሜታ አላቸው? የተሰኙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ

አበረታታቸው/ቻቸው፡፡

## አጭር ማብራሪያ መስጠት

መምህር! በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን በማስመልከት አጭር መብራሪያ ስጥ/ጪ፡፡

በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚያስፈልጉ የሥነ-ምግባር መርሆዎች ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መኖር፣ ሰብዓዊ መብትን ማክበር፣ እውነትን መያዝ፣ ምስጢር መጠበቅ፣ ለሰው ማሰብ፣ ፈቃደኝነት፣ እራስን መስጠትና በብቃት ማገልገል የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ማሕበራዊ አገልግሎት የሚባሉት ደግሞ ባለን ጉልበትና እውቀት የተቸገረን ሰው መርዳት፣ አካባቢን ማጽዳትና ማስዋብ፣ ለአዛውንቶች ቅድሚያ መስጠት፣ መማሪያ ክፍልን ማጽዳትና ከመማሪያ ክፍል ውጭ በተለያዩ ክበባት ውስጥ መሳተፍ፣ ለሕጻናት መጻሕፍትን መለገስ፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት ከጥፋትና ውድመት መጠበቅና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

7. ማጠናከሪያ፡- በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን በሚመለከት ዋና ዋና ሃሳቦችን ግለጽ/ጪ።

8.ምዘና፡- ተማሪዎች እንዲያገኙት የሚጠበቀውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት መጎናጸፋቸውን ለማረጋገጥ ተማሪዎችን ከማህበራዊ አገልግሎት ጋር የተያያዙ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን በቃል ጠይቃቸው/ቂያቸው።

**የተግባር 4.7 መልስ**

መምህር፡- ተማሪዎች ልንከተላቸው የሚገቡ የመንገድ ትራፊክ ደህንነቶችን ማለትም ከመኪና መንገድ ላይ መጫወት ወይም መሯሯጥን መተው፣ መንገድ ከማቋረጥ በፊት ግራና ቀኝ ማየት፣ መንገድ ስንሄድ የእግረኛ መንገድ ብቻ መጠቀም፣ መንገድ ስናቋርጥ በዜብራ ምልክት ላይ ብቻ መጠቀም፣ ከተፈቀደው ቦታ በስተቀር በሌላ ቦታ መንገድ ለማቋረጥ አለመሞከር፣ መንገድ ስናቋርጥ ሰዎችን ወይም ስልክ አለማናገር፣ በአደባባይ ላይ ፈጽሞ ለማቋረጥ አለመሞከር፣ ብስክሌት በምንነዳበት ጊዜ የብስክሌቱን ደህንነት ማረጋገጥ፣ ከመኪና ስንወርድ መኪናው በአግባቡ እስኪያቆም ድረስ መጠበቅ፣ እንዲሁም ቀስ ብሎ መውረድና የመሳሰሉትን ጥንቃቄች ማድረግ ከተማሪዎች እንደሚጠበቅ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

# የምዕራፉ መልመጃዎች መልሶች

## I. የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች መልስ

1. እውነት. 2. እውነት. 3. እውነት.5. እውነት.

## II. የአዛማድ ጥያቄዎች መልስ

1. ሐ 2. ሀ 3. ለ 4. መ 5. ሠ

## III.የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

1. መ 2.ሐ 3. ሐ 4. ሀ 5. ሀ

## IV. አጭር መልስ የሚሹ ጥያቄዎች መልስ

1. መልካም ባሕርይ

2.ለወላጅ መታዘዝ

3. ታማኝነት፣ ታላላቆችን ማክበር፣ ሃላፊነት መውሰድ፣ እውነተኛነት፣ በርትቶ ማጥናት፣ውጤታማ ምክርን ማዳመጥ

# ምዕራፍ 5፡ የመቻቻል ባሕል

(የተሰጠ ሰዓት፡- 18 ክፍለ-ጊዜ)

መግቢያ

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚያስፈልጉ ሥነ-ምግባሮችን ተምረዋል፡፡በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ የመከባበር ባህልን ምንነት፣ የመቻቻል ባህል አመላካቾች፣ የመቻቻል አስፈላጊነት፣ የመቻቻል ባህርያትና በመቻቻል ሒደት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ትማራላችሁ፡፡

የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች፡-

- የመቻቻል ባህልና ምንነትን መግለጽ፣
- የመቻቻል ባህል አመላካቾችን መከየት፣
- የመቻቻል ባህልን አስፈላጊነት መዘርዘር፣
- የመቻቻል ባህልን ማንጸባረቅ፣
- በመቻቻል ባህል ውስጥ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን መለየት፤

## 5.1. የመቻቻል ባሕል ምንነት

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- የመቻቻል ባህልን ምንነት መግለጽ፣
- የመቻቻል ባህልን በተግባር ማሳየት፣

1. አጠቃላይ ሁኔታ፡- በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የመቻቻል ባህልን ምንነት አጠንክረው ይማራሉ፡
2. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-ፎቶግራፎችና ሥዕሎች

3. የመማር ማስተማር ዘዴ፡-የቡድን ውይይት፣ ኡግዚቢሽን እና ቃለ-ምልልስ
4. **መግቢያ፡-** የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይዝ/ዢ።ያለፈውን ትምህርት በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አስታውስ/ሺ።.ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎናጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው።
5. አቀራረብ፡-

መምህር! የመቻቻል ባህል ምድን ነው? የመቻቻል ባህል ተግባራዊ የሚሆነው የት ነው? የተሰኙ የግንዛቤ ጥያቄዎችን ጠይቅ/ቂ።

☞ **መመሪያ፡- መምህር፡ ተማሪዎችን እያንዳንዳቸውን ጥያቄ በመጠየቅ እንዲያስቡበትና መልስ እንዲሰጡ አበረታታቸው/ቻቸው።.** ተማሪዎች እያንዳንዳቸው እነኚህን ሁለት ጥያቄዎች በግል፣ በመቀጠልም በቡድን ሰርተው ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ። በመጨረሻም ትክክለኛውን መልስ መስጠት አለመስጠታቸውን ድጋፍ አድርግላቸው/ጊላቸው።

**አጭር ማብራሪያ መስጠት**

☞ መቻቻል ልዩነትን በትእግስት በመቀበል በሰላም አብሮ መኖር ማለት ነው። መቻቻል በተለያዩ ደረጃዎች ለምሳሌ በቤተሰብ፣ በጓደኛ፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተ-እምነት፣ በኳስ ሜዳ ወዘተ. አብሮ መኖርና መከባበር እንዲሁም ለልዩነቶች እውቅና መሰጣጣትና አንዱ የሌላውን እሴትና ልማድ ማክበር እንደ ድልድይ የሚያገለግል ነው።

6. ማጠናከሪያ፡- ከመቻቻል ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ነጥቦችን በመከለስ ግለጽላቸው።
7. ምዘና፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ከሚፈለገው ብቃት ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ተግባር 5.1 ላይ ከተወያዩ በኋላ ሃሳባቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ አበረታታቸው/ቻቸው።

### የተግባር 5.1 መልስ

☞ መቻቻል ልዩነቶችን ማክበር፣ እውቅና መሰጣጣት፣ እሴቶችን፣ ልማዶችን፣ ፍቃደኝነትን፣ ባህና ቋንቋ የመሳሰሉትን ማህበረሰቡ የሚያከብራቸውንና የሚወዳቸውን ማክበርና እውቅና መስጠት ነው ብለው ሊመልሱ ይችላሉ።

## 5.2. የመቻቻል ባህል *መገለጫዎች*

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

✍ የመቻቻል አመላካቾችን ትለያለህ።

1. አጠቃላይ ሁኔታ፡-በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የመቻቻል ባህሎችን በመለየት ይማራሉ።
2. የትምህር መርጃ መሳሪያዎች፡-ቻርት በመጠቀም ማስተማር
3. የመማር ማስተማር ዘዴ፡-የግንዛቤ ጥያቄ፣ አግዚቢሽን፣ የቡድን ውይይትና ጽብረቃ
4. **መግቢያ፡-** የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይዥ/ዢ።ያለሰውን ትምህርት በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አስታውስ/ሺ።.ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎነጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው።

5. አቀራረብ፡-

መምህር! የመቻቻል ባህል አመላካቾች የትኞቹ ናቸው? የተሰኘውን የግንዛቤ ጥያቄ ጠይቅ/ቂ።

## አጭር ማብራሪያ መስጠት

☞ የመቻቻል ባህል አመላካቾች ከሆኑት ነገሮች መሃከል ጥቂቶቹ፡- የቋንቋዎች እኩልነት፣ የሕግ እኩልነት፣ የሃሳብ እኩልነት፣ የእምነት እኩልነትና ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች መሆናቸውና የመቻቻል ባህል ያለው ሕዝብ የተለያዩ ሕዝቦችን ባህልና ቋንቋ መንከባከብና ልዩነቶችን በእኩልነት በማክበር አብረው የሚኖሩ መሆናቸውን አስገንዝብ/ቢ። በተጨማሪም መቻቻል የተለያዩ አመላካቾች ማለትም እውቅና መሰጣጣትን፣ ተቀባይነት ማግኘት፣ መከባበርንና የሃሳብ መረዳዳት እውቅና መሰጣጣት መሆናቸውን ተማሪዎች በአጋባቡ እንዲገነዘቡ በማድረግ አበረታቸው።

6. ማጠናከሪያ፡- መቻቻልን የሚያመላክቱ ዋና ዋና አመላካቾችን በመከለስ በመተንተን ማብራራት

7. ምዘና፡-

☞ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች እንዲያገኙት የተፈለገውን ብቃት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ተግባር 5.2 በመስራት ከታች በቀረበው መሰረት ትክክለኛውን መልስ መስጠታቸውን በመመልከትና በማበረታታት የሰጡት መልስ እንደሚከተለው መሆኑን አረጋግጥ።

☞ **የ 5.2 መልሶች 1. ሐ 2. ለ 3. ሐ**

## 5.3. የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት

1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

✍ የመቻቻል ባህልን አስፈላጊነት መግለጽ፣

1. አጠቃላይ ሁኔታ፡-በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች የመቻቻል ባህልን አስፈላጊነት ይማራሉ፡፡
2. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡-ሥዕሎችና ፎቶግራፎች
3. የመማር ማስተማር ዘዴ፡-ውይይትና ክርክር በማካሄድ ማስተማር፣
4. መግቢያ፡- የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይጅ/ዢ፡፡ያለሰውን ትምህርት በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አስታውስ/ሺ፡.ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎነጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው፡፡
5. አቀራረብ፡-

   መምህር፡- መቻቻል ለምን አስፈለገ? የሚለውን የግንዛቤጥያቄ ጠይቅ/ቅ፡፡

### አጭር ማብራሪያ መስጠት

☞ በተማሪዎች የተሰጠውን መልስ ካዳመጥክ በኋላ አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ የመቻቻልን አስፈላጊነት ለተማሪዎች አስረዳ/ጂ፡፡ በአካባቢያቸው በሚገኙ ተጨባጭ ምሳሌዎች በመታገዝ አብራራላቸው/ሪላቸው፡፡ . በዚህ መሰረት መቻቻል ያስፈለገው ማሕበረሰቡ ግጭት የሚፈጠርባቸውን አጋጣሚዎች በመቀነስ ሰላም ለመፍጠር ስለሚረዳ ነው፡፡ በተጨማሪም የማሕበረሰቡን መረጋጋት፣

ተስፋና ሰላም በማስቀጠል በሰላም እንዲኖሩ ይረዳል፡፡ ለምሳሌ ከቤተሰባቸው፣ ከጎረቤት፣ ከጓደኛና በትምህርት ቤት ውስጥ በሰላም አብረው እንዲኖሩ የመከባበር ባህልን ማጎልበት ወሳኝ ነው፡፡

7. ማጠናከሪያ፡- የመቻቻልን አስፈላጊነት የሚመለከቱ ዋና ዋና ሃሳቦችን በመከለስ ተንትነህ አስረዳ፡፡

☞ መቻቻል ብዝሃ-ባህልን በማጎልበት ውስጥ ጉልበት ወይም ጥንካሬ መሆኑን ለተማሪዎች የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ በወደፊት ህይወታቸው ውስጥ እንዲጠቀሙበት ማበረታታት ጥሩ ነው፡፡

8 ምዘና፡-

☞ ከዚህ ትምህርት ማብቂያ በኋላ ተማሪዎች ከሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ተግባር 5.3 ስር የቀረበውን የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት ምድን ነው? የሚለውን ጥያቄ በቃል በመጠየቅ አረጋግጥ/ጪ፡፡

**የተግባር 5.3 መልስ**

☞ መቻቻል ማሕበረሰብ አብሮ እንዲኖር ያግዛል፡፡ያሉትን ልዩነቶች እንደ መልካም አጋጣሚ እንዲጠቀምና እውቅና ለመሰጣጣት ይረዳል፡፡ ሰላማዊና የተረጋጋ ኑሮ እንዲኖሩ ያግዛል፡፡ለምሳሌ ተማሪዎች ከቤተሰባቸው፣ ከጎረቤት፣ ከጓደኞቻቸውና ከትምህርት ቤታቸው ጋር በሰላም እንዲኖሩ ያግዛል፡፡ የማሕበረሰብን ሰላምና ፍቅር በማጎልበት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ በተጨማሪም ሕብረ-ባህላዊነት ተቀባይነት እንዲያገኝና እንዲጠናከር በማድረግ ማህበረሰቡ አብሮ ለመኖር ትዕግስትና ፍቅር እንዲኖረው ይረዳል፡፡

## 5.4. በመቻቻል ውስጥ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች

## 1.ተማሪዎች የሚጎጸፏቸው ዝግተኛ የመማር ብቃቶች፡-

- በመቻቻል ውስጥ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፤
- የመቻቻልን ባህርይ ያሳያሉ።

1. አጠቃላይ ሁኔታ ፡- በዚህ ትህርት ውስጥ ተማሪዎች በመቻቻል ባህል ላይ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ለይተው ይማራሉ።
2. የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡- ቻርቶች
3. የመማር ማስተማር ዘዴ፡- የግንዛቤ ጥያቄ፣ ውይይትና ገለጻ
4. መግቢያ ፡- የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ካለፈው ትምህርት ጋር አያይዥ/ዢ።ያለሰውን ትምህርት በሚመለከት ዋና ዋና ነጥቦችን አስታውስ/ሺ፡.ከዕለቱ ትምህርት በኋላ የሚጎነጸፉትን ዝቅተኛ የመማር ብቃት እንዲያውቁ ግልጽ አድርግ/ጊላቸው።
5. አቀራረብ፡-መምህር! በመቻቻል ባህል ውስጥ እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች ምን ምንድን ናቸው? የተሰኘውን የግንዛቤ ጥያቄ ጠይቅ/ቂ።

**አጭር ማብራሪያ መስጠት**

መልስ፡-በመቻቻል ባህል ውስጥ እንቅፋት የሚሆኑ በርካታ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ችግር በርካታ ሰዎች የመቻቻልንና መከባበርን ባህል በትምህርት ቤቶች፣ በማህበረሰቡ ውስጥና በየዕለት ተዕለት ተጨባጭ ህይወታቸው ውስጥ ተግባራዊ አለማድረግ ነው። አድልዎ፣ ትምክህት፣ ጥላቻ፣ ስም ማጥፋት፣ አለመቀራረብና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ የመቻቻል ባሕል እንቅፋቶች ናቸው የሚለውን ሀሳብ በአግባቡ በመገንዘብ መልስ መስጠት መቻላቸውን አረጋግጥ/ጪ።

6. ማጠናከሪያ ፡-በመቻቻል ባህል ውስጥ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን በመከለስ አብራራ/ሪ፡፡.

   ለምሳሌ አድልዎ፣ ትምክህት፣ ጥላቻ፣ ስም ማጥፋት፣ አለመቀራረብና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ የመቻቻል ባሕል እንቅፋቶች ናቸው፡፡

9 ምዘና፡-

☞ ከዚህ ትምህርት ማብቂያ በኋላ ተማሪዎች ከሚፈለገው የብቃት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ ተግባር 5.4 ስር የቀረበውን የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት ምድን ነው? የሚለውን ጥያቄ በቃል በመጠየቅ አረጋግጥ/ጪ፡፡

**የተግባር 5.4 መልስ**

1. አድልዎ፣ ትምክህት፣ ጥላቻ፣ ስም ማጥፋት፣ አለመቀራረብና የመሳሰሉት ዋና ዋናዎቹ የመቻቻል ባህል እንቅፋቶች ናቸው፡፡
2. መቻቻል

# የምዕራፉ መልመጃ መልሶች

**I. የእውነት/ሐሰት ጥያቄዎች መልሶች**

1. እውነት 2. ሐሰት 3. እውነት 4. እውነት 5. እውነት

II. የምርጫ ጥያቄዎች መልስ

1. ለ 2. መ 3.ለ

## III. የመውያያ ጥያቄዎች መልስ

1. በመቻቻል ባህል መሰረት ልዩነቶችን በትዕግስት መቀበል በሰላም አብሮ መኖር ማለት ነው። ልዩነቱም በሃሳብ፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በአመለካከትና በሌላም ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት ለልዩነቶቹ እውቅና መስጠትና ማክበር በሰላም አብሮ መኖር ማለት ነው። ለምሳሌ ሃገራችን በባህልና እሴት ልዩነት ውስጥ በመቻቻል አብሮ በመኖር ትታወቃለች። በሃገራችን ውስጥ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረ-ሰቦችና ሕዝቦች አብረው ይኖራሉ። እነኚህ ሕዝቦች የተለያዩ ማሕበራዊ ተግባራትን ማለትም ዓመት በዓላትን፣ ዝግጅቶችንና የተለያዩ ሥርዓቶቻቸውን እንደያዙ ተቻችለው ይኖራሉ።
2. የመቻቻል ባህል መጎልበት የሌሎች ሰዎችን ሃሳብ፣ አመለካከትና ተግባር በማክበርና በፍቅር በማየት ይጀምራል። ልዩነት ውበት መሆኑን በማመን እውቅና መሰጣጣት፣ መከባበር፣ ትዕግስትን መላበስና ሕብረ-ባህላዊነትን ማክበር፣ የማህበረሰቡን እሴቶችና ወጎች በማክበር የመቻቻል ባህልን መጎናጸፍ ይቻላል።

# ምዕራፍ 6፡ የባህል ብዝሃነትን ማክበር

**(የተመደበው ጊዜ፡ 18 ሰዓት)**

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች ፡-

- የባህል ብዝሃነት ምንነትን መግለጽ፣
- የባህል ብዝሃነት አስፈላጊነትን መዘርዘር፣
- ባህል ብዝሃነትን ማድነቅ።

## 6.1. የባህል ብዝሃነትን ማክበር

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የባህል ብዝሃነት ምንነትን መግለጽ፣
- የባህል ብዝሃነት ጥቅሞችን መዘርዘር፣
- የባህል ብዝሃነትን ማድነቅ።

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርትይዘት ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ብዝሃነትና መቻቻልን ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ስዕሎችንና ሚና በመጫወት ማስተማር

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የቡድን ውይይቶች፤ ማሳያዎችንና አስተያየቶችን መጠቀም። **መግቢያ፡** አዲሱን ርዕሰ ማስተዋውቅ እና ካለፉት

የትምህርት ይዘት ጋር ማጣጣም ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶችን መግለጽ ።

**የትምህርት አቅርቦት:** ለሚከተሉት ቃላት ትርጉሙን እንዲጽፉ የግንዛበቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀምር ፡-

- ብዝሃነት፡- የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣የልምድ እና የአሠራር ልዩነቶችን ያንጸባርቃል።
- የባህል ብዝሃነትን ማክበር ፡- ለባህሎች፤ ወጎች፤ ልምዶች እና በአጠቃላይ ልዩነትን ማክበር ፍትሃዊ ነው።
- መድልዎ፡- ሆን ብሎ አስቦበት ወይም በቸልተኝነት የሌሎችን መብቶችና ጥቅማጥቅሞች በመከልከል፤ ለሌሎች ደግሞ የማይገባውን ጥቅም መስጠት ነው ።

የባህል ብዝሃነት እንዴት ይፈጠራል? የባህል ብዝሃነት የሚፈጠረው የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች ወደ አንድ ቦታ ሲሰባሰቡ ነው። የባህል ብዝሃነት ማለት ብዙ ባህል ያለው ማህበረሰብ ማለት ነው።የተለያዩ ባህል ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ አመለካከቶች፣ ወዘተ የመሳሰሉ ያላቸው ማህበረሰቦች በአንድ ቦታ አብሮ መኖር ሲጀምሩ ባህላዊ ብዝሃነት ይፈጠራል። በክፍል ውስጥ አብሮ የሚማሩ ተማሪዎች የሃይማኖት፣ የቋንቋ እና የብሔር ልዩነቶች ሊኖራቸው ይችላል። ይህም የባህል ብዝሃነት ምሳሌ ሆኖ ሊገለጽ ይችላል።

በአገራችን ብዙ ቋንቋዎች ፤ የሃይማኖት ልዩነቶች፤ የተለያዩ ልምዶች እና ወጎች መኖራቸው ለባህል ብዝሃነት አርአያነቱ ተጨባጭ ምስክር ነው። የባህል

ብዝሃነት ያለው አገር እንደ የተለያዩ የእርሳስ ቀለሞች ያማረ ነው። ስለዚህ የባህል ብዝሃነትን ማክበር ለባህላዊ ልዩነቶች እና ልምዶች አዎንታዊ አመለካከትን ያሳያል።

**ማጠናከሪያ** ፡ ስለ ባህላዊ ብዝሃነት ዋና ዋና ነጥቦችን ማብራራት።

**ግምገማ ፡** ከአጠቃላይ ገለጻ በኋላ የሚከተሉትን የተግባር 6.1 ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎቹን የመረዳት ሁኔታ መገምገም፡-

**መመሪያ፡** - ተማሪዎችን ስለ ሃሳብ ብዙሃነት በመጠየቅ እና መልሶቻቸውን እንዲያደራጁ ማድረግ። ብዙሃነታችን ማራኪ፣ ከጭንቀት የጸዳ የትምህርት ቤት አካባቢን በመፍጠር ረገድ የራሱ ሚና እንደሚጫወት ለተማሪዎች ማስረዳት።

## የተግባር 6.1 መልሶች

1.የባህል ብዝሃነት በተለያዩ መንገዶች ልገለጽ ይችላል።ለምሳሌ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣በብሔር፣በአለባበስ፣በዘፈን፣በማህበራዊ መሰተጋብሮች እና በመሳስሉት ሊሆን ይችላል።

2. ልዩነቶችን አለመቀበል ለተለያዩ ችግሮች ሊያጋልጥ ይችላል። ለግጭቶች፤ አለመከባበር እና አለመቻቻል እንዲኖርና እንዲፈጠር ልያደርግ ይችላል ።

## 6.2. በባህል ልዩነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- በባህል  ብዙሃነት ውስጥ የአንድነትን አስፈላጊነትን መግለጽ፤
- በልዩነት ውሰጥ አንድነት ምን እንደሆነ ማብራራት።

**የትምህርቱ አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርትይዘት ፣ ተማሪዎች በልዩነቶች ውስጥ የአንድነት ምንነትን ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** ስዕሎችንና ፖስተሮችን መጠቀም

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**:የቡድን ውይይቶች፤ ማሳያዎችንና አስተያየቶችን በመጠቀም።

**መግቢያ፡**የዕለቱን የትምህርት ርዕሰ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ማስተዋውቅና ካለፈው የትምህርት ይዘት ጋር ማገናኘትና ማጣጣምና ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ  የመማር ብቃቶችን መግለጽ።

**የትምህርት አቅርቦት፣** እነዚህን የግንዛበቤ ጥያቄዎችን  በመጠየቅ መጀመር ፡

- በባህል ብዙሃነት  ውስጥ አንድነት ለምን እንደሚያስፈለግና በመማርያ መጽሐፍ  ውስጥ ካለው ምስል ምን እንደተረዱ መጠየቅ

**መመሪያ**:ተማሪዎችን በአንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ  መጠየቅ እና  እንዲመልሱ ማበረታታት። እያንዳንዱ ተማሪ ሁለቱንም ጥያቄዎች መጀመሪያ በግል ከዚያም በቡድን እንዲሰሩ ማድረግ ፣በመጨረሻም ምላሻቸውን ለክፍል ማቅረብ እንዳለባቸው ማስገንዘብ።  7.ማጠናከሪያ ፡- ዋና ዋና ነጥቦችን በማብራራት ትምህርቱን ማጠናከር። የመቻቻል ባህል ማለት የሌሎችን

አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ተግባር ማክበር ነው። የመቻቻል ባህል ከእኛ ጋር ለሚኖሩ ወይም ለሚሰሩ ሰዎች አመለካከት፣ እምነትና ተግባር ፍትሃዊ እና ጥሩ አመለካከት እንዲኖረን ይረዳናል።

**ግምገማ፡** ከአጠቃላይ ገለጻ በኋላ የሚከተሉትን የተግባር 6.2 ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማርዎቹን የመረዳት ሁኔታ መገምገም፡-

## የተግባር 6.2 ጥያቄዎች መልስ፤

1. ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ያሉንን ልዩነቶች ማክበር ለመማር ማስተማር ጤናማ አካባቢ እንዲፈጠር ይጠቅማል።

2. በብዝሃነት ውስጥ አንድነትን ሳንጠብቅ የተሳካ ትምህርት አሰጣጥን መጠበቅ አንችልም። ምክንያቱም የሌሎችን ሀሳቦች፤ እምነቶችንና ባህሎችን ካላከበርን መረጋጋት፤ ሰላም እና የመማር ማስተማር ዓላማና ግብ አይረጋገጥም።

3.በባህል ብዝሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት፤- ተማሪዎች በትምህርት ቤት፣ ሰዎች በሥራ ቦታ እና በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጨምር ይረዳል፣ በግለሰቦች መካከል ያለውን ግንኙነትና ትብብር ለማሻሻልም ወሳኝ ሚና አለው፡ እንዲሁም ውጤታማነትን ያሻሽላል፣የስራ ጥራትን፣ ምርታማነትንና የአኗኗር ዘይቤን ለማሻሻልም ይረዳል።

## 6.3. በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል ጥቅሞች

ተማሪዎች እንዲጎናጸፏቸው የሚጠበቁ የመማር ብቃቶች፡-

- የመቻቻል ጥቅሞችን መግለጽ።
- የሌሎችን ሰዎች  ባህል ማክበር።
- የባህል ልዩነቶችን ማድነቅ።

**አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርት ተማሪዎች በልዩነት ውስጥ  የመቻቻል ጥቅምን ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** የመማሪያ መጽሐፍ

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: የቡድን ውይይት፣ የጉዳይ ጥናትና ምልከታ

**መግቢያ፡** ከዕለቱ የትምህርት ርዕስ ጋር ማስተዋወቅ እና ካለፉት የትምህር ይዘቶች ጋር ማገናኘት።

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡-**የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ፤

- የባህል ብዝሃነትና የመቻቻል አስፈላጊነትን እንዲያብራሩ ማድረግ።

**መመርያ፡** ስለ ብዝሃነትና የመቻቻል አስፈላጊነት ተማሪዎችን መጠየቅ።

ንባብ፡- ስለ መቻቻል ባህል

መቻቻል ማለት አንድን ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ  ባሉበት ሁኔታና አክብሮት ማስተናገድ ነው። የሌሎችን እምነት፣ የኑሮ ዘይቤንና አመለካከት ማክበር ማለት ነው። ይህም እርስ በርስ ለመከባበር፣ ለመረዳዳት፣ ለመተሳሰብ፣ ለመማማር፣ በሰላም አብሮ ለመኖር፣ ልማትን ለማፋጠን፣ ፍቅርን ለማጠናክር ያግዛል። የኦሮሞ ህዝብ የተለያዩ ብሔር ፤ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ባህል በማክበርና እውቅና በመስጠት ይታወቃል። በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ እንኳን የሰው

ልጅ ባህል የዱር አራዊትም ይከበራሉ። ይህ የሕዘቡ እሴት፡መታወቂያ እና ጨዋነት ነው።

ስለ ትምህርት ቤት ጓደኞች ታርክ

ከተማሪዎች ውይይት በኋላ የተለያዩ ሃይማኖትን የሚከተሉና በመቻቻል በፍቅር አብሮ ስለሚኖሩ ተማሪዎች ላይ ተጨማሪ ገለጻ መስጠት ።

**ክለሳ**፡ ዋና ዋና ነጥቦቹን በማጠቃለል።

***ግምገማ፡*** በዚህ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎችን በመጠየቅ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መገምገም።

## የተግባር 6.5 ጥያቄ መልሶች

1. ልዩነት አብሮ መኖርን ይገድባል? አይ

2. ከኢፍቱ፣ ቶሎላሳ እና ቀጄላ ድርጊት ምን ምን ተማራችሁ? በልዩነት ውስጥ በአንድነትና በፍቅር አብሮ መኖር እንደሚቻል።

ተግባር 6.6

1. ከዚህ ታሪክ ምን ተማራችሁ? በልዩነት በአንድነትና በፍቅር አብሮ መኖር መቻልን።

2. ይህ ትረካ ለብዝሃነት አክብሮት የሚያሳየው እንዴት ነው? አንዱ የሌላውን ባህል በማክበር እና የእርስ በርስ ደስታን አብሮ በመካፈል።

## 6.4. የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ

ከተማሪዎች የሚጠበቁ  የመማር ብቃቶች፡-

- የባህል ብዝሃነትን ማድነቅ።
- የባህል ብዝሃነትን ማክበር።

**አጠቃላይ እይታ፡** በዚህ ትምህርት ይዘት ውስጥ ተማሪዎች ስለ ባህል ብዝሃነት ይማራሉ።

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፡** የመማሪያ መጽሐፍ

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**: ርፖርት እና ምልከታ

**የዕለቱን ትምህርት ማቅረብ፡** የግንዛቤ ጥያቄዎችን መጠየቅ።ለምሳሌ፣

- በክፍል ውስጥ የባህል ብዝሃነትን እንዴት ታስተናግዳለህ/ሽ?

**መመርያ፡** መጀመሪያ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የባህል ብዝሃነትን እንዴት እንደሚያስተናግዱ መጠየቅና  ተማሪዎች የእነዚህን ነጥቦችና ሐሳቦች ማጠቃለያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ተማዎችን መምራት። ሁሉም ተማሪ እንዲሳተፍ መበረታታት አለባቸው።

**ንበብ**፡ የእንግዳ ተቀባይነት ባህል ምን እንደሆነ አስረዳ።

የሚንኖርበት ዓለም በልዩነት የተሞላች ናት። ይህ ልዩነት ተፈጥሯዊ ነው። ይህንን ተፈጥሮአዊ ልዩንት መቀበል አስፈላጊ ነው። የሀገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችም የራሳቸው የሆነ  ባህል አላቸው። ለረጅም ዘመናት

አንዱ የሌላውን ባህል በማክበር አብረው ኖረዋል:: ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ የመከባበር፣ የመረዳዳት፣ የመተባበርና በራስ የመተማመን ባህላቸውን በማሳደግ የመግባባት ባህልንም ፈጥሮላቸዋል።

የባህል ብዝሃነት ለትምህርት ቤት ውበት ነው። ከተለያዩ ባህል የመጡ ተማሪዎች ሲሰባሰቡ ቋንቋን፣ አዲስ እውቀትን፣ የአስተሳሰብ መንገዶችንና ልምዶችን ይጋራሉ። በአጠቃላይ ትምህርት ቤት የባህል ብዝሃነት ሲኖረው ከተለያዩ ብሔሮች፤ ብሄረሰቦችና ሕዝዘቦች ባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት ጋር ለመላመድ ዕድል ይሰጣል።

**ክለሳ፡** ዋና ዋና ነጥቦቹን በመከለስ የእለቱን ትምህርት ማጠቃለል።

**ውስን ጥናት፡-** ባህላዊ ጭፈራ

ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ጭፈራ እንዲያነቡ ማድረግ ። የተለያዩ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ባህላዊ ሙዚቃ እና ጭፈራ እንዲማሩ፣ እንዲያከብሩና እንዲቀበሉ ማሳየት።

ግምገማ፡ በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ የተግባር ጥያቄዎችን ተወያይቶበት ለክፍል ጓደኞቻቸው ተማሪዎች ያቅርቡ:: ከተማሪዎች ገለጻ በኋላ እርማትና ማጠቃለያ ሐሳብ መስጠት።

የተግባር 6.7 ጥያቄ መልሶች

በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያዩ።

1. የባህል ብዝሃነት ማለት ምን ማለት ነው? ለተለያዩ ብሔሮች ባህል እውቅና በመስጠት በሰላም አብሮ መኖር::

2. ብዝሃነትን መቀበል ለማህበራዊ ትስስር አስተዋፅኦ አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

የክለሳ ጥያቄ መልሶች

መመሪያ I: እውነት ወይም ሐሰት

1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት

መመሪያዎች II. እራስህን/ሽን ገምግም/ሚ። የተማሪዎቹን አስተያየት በመቀበል ማጠቃለል።

ትዕዛዝ III. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. በሰላም አብሮ መኖር አዳዲስ ሀሳቦችንና አመለካከቶችን እርስ በርስ ለመማማር ዕድል ይሰጣል፣ ከተለያየ ባህል ካላቸው ሰዎች ክህሎትና እና እውቀትን ማግኘት ያስችላል፤ ለባህላዊ ቅርስ፣ ለኪነጥበብ ወዘተ እውቅና ለመስጠት መንገድ ይከፍታል።

2. እኩልነትን በማስተማር፣ብዝሃነትን በመረዳት፣ በማክበር፣ በመቀበል፣ በማሳየትና በመሳተፍ አድልዎን መቀነስ ወይም ማቆም እንችላለን።

# የግብረገብ ትምህርት 4ኛ ክፍል መርሃ ትምህርት

**ምዕራፍ 1፡ ራሰን መሆንን ማጎልበት (የተመደበው ጊዜ፡20 ሰዓት)**

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡**

የራስ መሆንን ትርጉም መግለጽ፣

የራስ መሆንን አስፈላጊነት መግለጽ፣

ራስን መሆንን የሚያጠናከሩ ዘዴዎችን መለየት፣

ራስን የመሆን ባህሪያት ማሳየት፣

ችግር ፈቺ ክህሎቶችን ማዳበር፣

ራስን ያለመሆን የሚያስከትለውን ውጤት መለየት።

| ብቃት | ይዘት | የማስተማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ራስን የመሆንን ምንነት ትገልፃለህ/ሽ።<br><br>ለራስ ከፍ ያለ ግምትን ለመጨመር የሚረዱ ዘዴዎችን ትዘረዝራህ/ሽ።<br><br>ራስን የመሆን ባህሪያትን ይዘርዘራሉ፣ | 1.1. ራስን መሆን<br><br>1.2 ራስን የመሆን ባህሪያት<br><br>• ራስን መቻል | •ራስን የመሆንን ምንነት በቡድን ይወያዩበት<br><br>•ራስን የመሆን ባህሪያት ላይ ለተማሪዎች የቡድን ስራ | • ተማሪዎች ራስን መሆን ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ<br><br>• ከተቀመጠው ብቃት ጋር በማዛመድ የተማርዎችን ስራ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| በራስ የመተማመንን ባህሪያትን ያሳያሉ።<br><br>ራስንየመቻል ምንነት ይገልጻሉ፣<br><br>በራስ የመተማመንን ምንነት ይገልጻሉ፣<br><br>ራስ የመግዛትን ምንነትን ይገልጻሉ<br><br>በራስ የመተማመን ባህሪያትን እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ ትገልጻለህ/ሽ<br><br>በራስ የመተማመን ባህሪያትን ታሳያለህ/ሽ<br><br>ራስን የመሆንን አስፈላጊነት ያደንቃሉ።<br><br>ተግዳሮቶችን መቋቋም የሚያስችሉ ችሎታዎችን ማዳበር<br><br>ችግሮችን የመቋቋም ችሎታ ማሳየት<br><br>ራስን ያለመሆን የሚያስከትለውን ተጽዕኖ መግለጽ፤<br><br>በራስ መተማመን የሌላቸውን ሰዎች ባህሪያትን መለየት። | • በራስ መተማመን<br><br>• ራስን መግዛት<br><br>1.3. ራስን መሆንን ማዳበር የሚቻልባቸው መንገዶች<br><br>1.4. በራስ የመኩራት ጥቅሞች<br><br>1.5. ችግሮችን የመቋቋም ችሎታዎች<br><br>1.6. ራስን ያለመሆን ውጤቶች | መስጠት<br><br>• ራስን መሆንን ማዳበር የሚቻልባቸው መንገዶች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br><br>• ራስን የመሆን ጥቅሞች ላይ በቡድን በመወያየት ሀሳባቸውን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረግ<br><br>• ተማሪዎች ችግሮችን የመቋቋም ችሎታዎች ላይ ሁለት ሁለት ሆነው በቡድን እንዲወያዩ ማድረግ<br><br>• ተማሪዎች ራስን ያለመሆን ችግሮችና ውጤቶች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ | መመልከት<br><br>• ጥያቄና መልስ<br><br>• ለተጠየቁት ጥያቄ የተማሪዎችን መልስ በመከታተል እርምት መስጠት<br><br>• የቤት ስራ መስጠት |

**ምዕራፈ 2፡ ሰብአዊ መብቶች (የተመደበው ጊዜ፡21 ሰዓት)**

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-

- የሰብአዊ መብት መከበር አስፈላጊነትን መግለፅ፣
- በመብቶች እና ኃላፊነቶች መካከል ያለውን ግንኙነት መለየት፣
- ሰብዓዊነትን ማክበር፣
- የህጻናት፤ የሴቶች እና አካል ጉዳተኞችን፣ መብቶች መግለጽ፣
- ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ባህሪን ማሳየት።

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የማስተማር ዘዴ** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| ሰብአዊ መብቶችን ትገልጻለህ/ሽ።<br><br>የሰብአዊ መብቶች ምሳሌዎችን ትናገራለህ/ሽ።.<br><br>ሰብአዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት ትዘረዝራለህ/ሽ<br><br>ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ዋጋ ትሰጣለህ/ሽ። | 2.1. የሰብዓዊ መብቶች ምንነት<br><br>2.2. የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት<br><br>2.3. ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች | • ስለ ሰብዓዊ መብቶች በውስን ገለጻ ውይይት ማድረግ<br><br>• የሰብዓዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ላይ ተማሪዎች እንድዲወያዩበት ማድረግ | • ተማሪዎች ሰብኣዊ መብቶች ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልጹ ማድረግ<br><br>ተማሪዎች<br><br>• የተማሪዎችን ስራ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎችን ያነጻጺራሉ።<br>ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎችን ይዘረዝራሉ።<br>.በመብቶች እና ግዴታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ይገልጻሉ።<br>ሰብአዊ ክብርን መግለጽ።<br>ሰብአዊነትን ማክበር።<br>ሰብአዊ መብት ጥሰትን ማውገዝ።<br>የሕፃናት መብቶችን መዘርዘር<br>መብቶችን መተግበር<br>የሴቶችን መብት መዘርዘር።<br>የሴቶችን መብት ማክበር።<br>የአካል ጉዳተኞችን መብቶች መዘርዘር።<br>የአካል ጉዳተኞችን መብቶች ማክበር። | 2.4. ሰብአዊ ክብር<br>2.5. የሕፃናት መብቶች መከበር<br>2.6. የሴቶች መብት መከበር<br>2.7. የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር | • ሰብአዊ መብቶች እና ግዴታዎች<br>ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ<br>• ተማሪዎች በሰብኣዊ ክብር ላይ ይወያዩበት<br>ሰለ የሕፃናት መብቶች መከበር፣. የሴቶች መብት መከበር፣<br>የአካል ጉዳተኞች መብቶች መከበር በድራማ መልክ ያማብራራት ። | ከተቀመጠው ዓላማና ግብ ጋር በማነጻጸር የተማሪዎችን ስራ ማየት<br>• ጥያቄና መልስ<br>• ለተጠየቁት ጥቄዎች የተማሪዎችን መልሶች በመከታተል ግብረ መልስ መስጠት |

## ምእራፍ 3: ሰላም (የተመደበው ጊዜ: 19 ሰዓት)

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-**

- የሰላምን ምንነት ማብራራት፣
- ለሰላም አስፈላጊነት ትኩረት መስጠት፣
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የአፈታት ዘዴዎችን ማድነቅ፣
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ችሎታን ማሳየት፣
- የሰላም እጦት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መለየት።

| ብቃት | ይዘት | የማስተማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የሰላም ምንነትን መግለጽ<br><br>የሰላምን አስፈላጊነት መዘርዘር።<br><br>የሰላምን አስፈላጊነት ማድነቅ።<br><br>ሰላምን ለማስፈን የሚረዱ መንገዶችን ትለያለህ/ሽ።<br><br>የሰላም እጦት የሚያስከትለውን ጉዳት መዘርዘር።<br><br>የግጭት አፈታት ምንነትን መግለጽ;<br><br>ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ዘዴዎችን መዘርዘር። | 3.1. ሰላም ምንነት<br><br>3. 2. የሰላም አስፈላጊነት<br><br>3.3. ሰላም የሚሰፍን የሚረዱ መንገዶች<br><br>3.4.ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት<br><br>3.5. የሰላም እጦት የሚያመጣው ጉዳት | • ተማሪዎች የሰላምን ምንነት ሁለት ሁለት ሆነው በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ<br><br>• ተማሪዎች የሰላምን አስፈላጊንት በቡድን እንዲወያዩበት ማድረግ<br><br>• ተማሪዎች ግጭትን በሰላማዊ መንገድ መፍታት በድራማ መልክ እንዲያሰዩ ማድረግ<br><br>• የፕራምድ ዘዴን በመጠቀቄም በሰላም እጦት የሚመጣውን ጉዳት እንዲወያበት ማድረግ | • ተማሪዎች ሰላምና ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲናገሩ መጠየቅ<br><br>•የተማሪዎችን ስራ ከተቀመጠው የመማር ብቃት እና ግቦች ጋር በማገናኘት መመልከት<br><br>•ጥያቄና መልስ<br><br>• ለተጠየቁት<br><br>ለተጠየቁት ጥያቂዎች የተማሪዎችን መልስ በመከታተል ግብረ መልስ መልስ መስጠት። |

## ምዕራፍ 4፡ በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚያስፈልግ ሥነ-ምግባር

**(የተመደበው ጊዜ: 21 ሰዓት)**

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች ፡-

የሥነ-ምግባርን ፍቺ  መግለጽ፣

ሥነ-ምግባር በማሕበራዊ ህይወት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት መግለጽ፣

የእረፍት  ጊዜን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ መግለጽ፣

በማሕበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት መለየት፣

ለመንገድ ትራፊክ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን መለየት፣

በማሕበራዊ አገልግሎቶች ውስጥ አስፈላጊ ለሆኑ የሥነ-ምግባር መርሆች ቦታ መስጠት።

| **ብቃት** | **ይዘት** | **የማስተማር ዘዴ** | **ምዘና** |
|---|---|---|---|
| የሥነ-ምግባርን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ፤<br>በክፍል ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ትዘረዝራለህ/ሽ..<br>መልካም ሥነ-ምግባር በማሕበራዊ ህይወት ውስጥ ያለውን አስፈላጊነት ትለያለህ/ሽ፤<br>መልካም ተግባራት የሚገለጹባቸውን መንገዶች ትዘረዝራለህ/ሽ።<br>የእረፍት ጊዜን በአግባቡ ስለመጠቀም ታስረዳለህ/ሽ፤<br>የእረፍት ጊዜን በአግባቡ የመጠቀምን አስፈላጊነት ትለያለህ/ሽ።<br>በማሕበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት ትለያለህ/ሽ፤<br>ተቀባይነት የሌላቸውን ተግባር በመፈጸም ሊከሰቱ የሚችሉትን ጉዳቶች ትገልጻለህ/ሽ።<br>የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ምንነት ትናገራለህ/ሽ፤<br>ልንከተላቸው የሚገቡ የመንገድ ትራፊክ ደንቦችን ትለያለህ/ሽ።<br>በማሕበራዊ አገልግሎቶች ውስጥ የሚፈለጉ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ትለያለህ/ሽ። | 4.1. የሥነ-ምግባር ምንነት<br>4.2. በማሕበራዊ ህይወት ውስጥ የሥነ-ምግባር አስፈላጊነት<br>4.3. የዕረፍት ሰዓትን በአግባቡ መጠቀም<br>4.4 በማሕበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን ተግባራት<br>4.5. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት<br>4.6. በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚፈለጉ የሥነ-ምግባር መርሆዎች | •በውስን ገለጻ ተማሪዎች በመልካም ሥነ-ምግባር ምንነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ተማሪዎች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የመልካም ሥነ-ምግባር አስፈላጊነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ.<br>• ሁሉም ተማሪ፡<br>• የትርፍ ሰዓት ምንነት<br>***• በማሕበራዊ ህይወት ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና የሌላቸው ተግባራት***<br>***•ስለ መንገድ ትራፊክ ደህንነትና***<br>• በማሕበራዊ አገልግሎት ውስጥ የሚፈለጉ የሥነ-ምግባር መርሆች ላይ እንዲወያዩበት ማድረግ | • ተማሪዎች መልካም ሥነ-ምግባር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እነዲናገሩ መጠየቅ<br>•የተማሪዎችን ስራ ከተቀመጠው ብቃትና ውጤጤት ጋር በማዛመድ መገምገም<br>•ጥያቄ እና መልስ<br>• ለተጠየቁት ጥያቄ የተማሪዎችን መልስ በመከታተል እርማት መስጠት። |

## ምዕራፍ 5: የመቻቻል ባህል (የተመደበው ጊዜ፡ 18)

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች:-

- የመቻቻልን ምንነት መግለጽ
- የመቻቻል አመላካቾችን መለየት
- የመቻቻልን አስፈላጊነት መዘርዘር
- የመቻቻልንባህርይ ማንጸባረቅ
- ለመቻቻል ባህል መዳበር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን መለየት

| ብቃት | ይዘት | የማስተማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የመቻቻል ባህልን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ፤.<br><br>የመከባበርን ባህል በተግባር ታሳያለህ/ሽ።<br><br>የመቻቻል ባሕል አመላካቾችን ትለያለህ/ሽ<br><br>የመቻቻል ባሕልን አስፈላጊነት የባሕል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን ትዘረዝራለህ/ሽ<br><br>የመቻቻል ባሕርይን ታንጸባርቃለህ/ሽ።<br><br>ገልጽለህ/ሽ፡<br><br>ለመቻቻል | 5. 1. የመቻቻል ባህል ምንነት<br><br>5.2. የመቻቻል ባሕል መገለጫዎች<br><br>5.3. የመቻቻል ባህል አስፈላጊነት<br><br>5.4. ለመቻቻል ባሕል እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮች | የግንዛቤ ጥያቄ<br><br>የመቻቻል ምንነትን መግለጽ<br><br>ተማሪዎች ስለመቻቻል ባህል እንዲወያዩበት ማድረግ<br><br>ማሳየት፣ የተለያዩ ጨወታዎችና ውስን ጥናቶችን መጠቀም<br><br>ተማሪዎች የመቻቻል ባሕል አስፈላጊነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br><br>የመቻቻል ባህል ጥቅሞችና ባለመቻቻል በሚከሰቱ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች እንዲከራከሩ መድረግ<br><br>የመቻቻል ባህል እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች  እንዲወያዩ ማድረግ, | የመቻቻል ባህል ምንነትን ተማሪዎች እንዲናገሩ መጠየቅ<br><br>የተማሪዎችን ትግበራ፣ ሚና መወጣት በማየት ከተቀመጠው ብቃት ጋር መመዘን<br><br>ጥያቄ እና መልስ በመጠቀም የተቀመጠውን ብቃት መመዘን<br><br>የተማሪዎችን መልስ በመከታተል ግብረመልስ መስጠት |

## ምዕራፍ 6፡ የባህል ብዝሃነትን ማክበር (የተመደበው ጊዜ፡ 18 ሰዓት)

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-

- የባህል ብዝሃነት ምንነትን መግለጽ
- የባህል ብዝሃነት አስፈላጊነትን መዘርዘር፣
- የባህል ብዝሃነትን ማድነቅ።

| ብቃት | ይዘት | የማስተማር ዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የባህል ብዝሃነት ምንነትን መግለጽ፣<br>የባህል ብዝሃነት ጥቅሞችን መዘርዘር፣<br>የባህል ብዝሃነትን ማድነቅ።<br>በባህል ብዙሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነትን መግለጽ፤<br>በልዩነት ውሰጥ አንድነት ምን እንደሆነ ማብራራት።<br>•የመቻቻል ጥቅሞችን መግለጽ።<br>• የሌሎችን ባህል ማክበር።<br>•የባህል ልዩነቶችን ማድነቅ።<br>•የባህል ብዙሃነትን ማድነቅ።<br>•የባህል ብዝሃነትን ማክበር። | 6.1. የባህል ብዝሃነትን ማክበር<br>6.2. በባህል ብዝሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነትን<br>6.3. በባህል ብዝሃነት ውስጥ የመቻቻል ጥቅሞች<br>6.4. የባህል ብዝሃነትን ማስተናገድ | ተማሪዎች የባህል ብዝሃነት ምንነተ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>ተማሪዎች በባህል ብዝሃነት ውስጥ የአንድነት አስፈላጊነት ላይ እነዲወያዩ ማድረግ<br>ከተማሪዎች ውይይት በኋላ ግብረ መልስ መስጠት<br>ተማሪዎች በምልከታ፣በጨወታ እና በትግበራ ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ | ምልከታና ውይይት<br>ክትትል፣ገለጻ፣ክርክር፣ የተማሪዎችን የተግባር ስራና ሚና መወጣት በማየት<br>ከተቀመጠው ብቃት ጋር ማመዛዘን<br>ጥያቄና መልስን በመጠቄም የተቀመጠውን ብቃት መመዘን<br>መልመጃዎችና ፕሮጀክቶች<br>የተማሪዎችን መልሶች በመከታተል<br>የማስተካከያ መልስ መስጠት |